# ይህ መልከ ጼዴቅ ማነው?

ለጸሎት ራሳችንን ዝቅ እናድርግ።

ውድ የሰማይ አባት ሆይ፡ ይህንን **እመን ብቻ** የሚለውን መዝሙር ስንሰማ፡ የእግዚአብሔርን ተስፋዎች ሁሉ ለመውረስ ማድረግ ያለብን ነገር ቢኖር፡ እነርሱን ማመን ብቻ እንደሆነ እንድናውቅ ያደርገናል። “ለሚያምን ሁሉ ይቻላል፡” ተብሎ ተጽፏልና። የሚጥል በሽታ ያለበት ልጅ እንደነበረው ሰው፡ “ጌታ ሆይ፡ አምናለሁ! አለማመኔን እርዳው፡” ብለን እንጮኻለን።

2 ስለ ታላቅ ኃይልህ፡ በዚህ በመጨረሻው ዘመን ራስህን ለእኛ ስለገለጥክበት ታላቅ መገለጥ እናመሰግንሃለን። ባለፉት ዘመናት እንዳደረገውና ለዚህም ዘመን ተስፋ እንደሰጠው፡ በአካላዊና በቁሳዊ ማስረጃዎች መልሶ የሚያጸናውን፥ ሕያው እግዚአብሔርን፡ እንዳገኘን ማወቃችን፡ ልባችንን እጅግ ደስተኛና፡ ሐሴት የተሞላ ያደርገዋል። አምላካችን ሆይ፡ እጅግ እናመሰግንሃለን። ማንም ወዴት መሄድ እንዳለበት በማያውቅበት በዚህ በጨለማ ዘመን፡ የመጠጊያና፡ የደህንነት ስፍራን ስላገኘን እጅግ ደስ ብሎናል።

3 አሁን ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ ስለ ቃልህ ስንናገር ባርከን። የተሰጡንን ተስፋዎች፡ በልባችን እንድናሳድጋቸው፡ በአክብሮት እንድንከባከባቸው፡ እንዲሁም በእውነተኛ እግዚአብሔራዊ ስነ ምግባር እንድንታዘዛቸው አድርገን። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለንና። አሜን።

4 [አንድ ወንድም ለወንድም ብራንሃም ተናገረ—እርታዒ።] (ኦህ፡ ይህን ማድረግ አልነበረባቸውም። የፍቅር ስጦታ? ይህን ማድረግ አልነበረባቸውም። እንዲህ ማድረግ አልነበረባቸውም። ማን ነው ያደረገው? ያደረግከው አንተ ነህ? ) ሥራ እስኪያጇን እየተቆጣሁት ነበር። ለእኔ የፍቅር ስጦታ እንደሰበሰበ ነገረኝ። ይህን ማድረግ አልነበረበትም። ይህንን አደንቀዋለሁ፡ እግዚአብሔር ያውቃል፡ ነ—ነገር ግን እኔ ለዚህ አልመጣሁም። አመሰግናለሁ። ጌታ ይባርካችሁ። የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ። ቀጥታ ለውጭ ሀገር ሚሲዮኖች አስቀምጣለሁ፡ በዚህም ለእግዚአብሔር መንግሰት እንደሚውል አውቃለሁ። የጌታ ፈቃድ ቢሆን ደግሞ፡ በዚህ ሳምንት ተቀምጣችሁ፡ ስትሰሙት የነበረውን፡ ይኸው ወንጌል ይዤ፡ ወደ ሌላ ሀገራት በምሄድበት ጊዜ፡ ራሴ እወስደዋለሁ፡ በዚያን ጊዜ እናንተ ባመናችሁበት መንገድ በስራ ላይ እንደሚውል አውቃለሁ። ይህን እንዳደርግ ጌታ ይርዳኝ።

5 በዚህ ሳምንት ለነበረው ታላቅ ተሳትፎ፡ እንዲሁም ዛሬ ማታ በ—በቴሌፎን መስመር ስላላችሁ ሰዎች ሁሉ እጅግ አመስጋኝ ነኝ። ለያንዳንዳችሁም ምስጋናችን ላቅ ያለ ነው።

6 ቢሊ ዛሬ ጠዋት ነገረኝ፡ እንዲህ አለኝ፡ “አባዬ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ጎህ ሲቀድ፡ በማለዳ ከእኔ ጋር መጥተህ ቢሆን ኖሮ፡ በዚህ አካባቢ ቆመህ እናቶች ልጆቻቸውን በመኪና ውስጥ ሲያጠቡ፡ እነዚያ ምስኪን ሰዎች በሮች እስኪከፈቱ ድረስ፡ በዝናብ ውስጥ ተቀምጠው ሲጠብቁ ታያቸው ነበር!”

ከእውነት ውጪ ሌላ ነገር ብነግራችሁ ምን ዓይነት ግብዝ እንደምሆን እያችሁ? በእውነት መጥፎ ሰው እሆን ነበር። አንዳንድ ጊዜ እናንተን ማሳዘን አለብኝ፡ ነገር ግን ፈልጌ አይደለም፡ ምክንያቱም... እናንተን የማሳዝነው እኔ አይደለሁም። የሚያሳዝነው እውነቱ ነው። እ—እኔም... ነገር ግን እናንተ የምትመጡት ለዚህ እንደሆነ አምናለሁ፡ ምክንያቱም ለእናንተ እጅግ ቅን ነኝ፡ እናንተንም ለመርዳት የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ። ጌታ እያንዳንዳችሁን ይርዳችሁ።

7 አሁንም ለሰጡን መልካም-ትብብር ሰዎችን ማመስገን እፈልጋለሁ፡ ይህንን የትምህርት ቤት ህንፃ፡ አዳራሹንና፡ ጂምናዚየሙን እንድንከራይ ለፈቀዱልን፡ የከተማው ነዋሪዎችንም ጭምር፡ ማመስገን እፈልጋለሁ። ባለስልጣናት እዚህ ካላችሁ እናንተንም ማመስገን እፈልጋለሁ። እንዲሁም ይህንን እንድናገኝ ስለረዳንና፡ በየምሽቱ ከእኛ ጋር በመሆኑ፡ ስለ መልካም-ትብብሩ የዚህ ሰፍራ ጠባቂ የሆነውን ተርሰተን ኮልቪንን ማመስገን እፈልጋለሁ።

8 የጀፈርሰንቪል ፖሊስ ኃይል እዚህ መጥተው፡ እጅግ በጣም ርካሽ በሆነ ክፍያ ጥበቃ ስላደረጉልን እናመሰግናለን። በሰዓት ሁለት ዶላር አካባቢ ይመስለኛል፡ ፖሊሶቹ እዚህ ልዩ ግዳጅ ላይ የተመደቡት፡ መኪኖችን ፓርክ ለማድረግ፡ ምንም ነገር... ምንም እንዳይፈጠርና፡ ሁሉም ነገር ሰላም መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። ለዚህም ሰዎችን እናመሰግናለን። እንዲሁም፡ እ—እዚህ ቦርዱ ላይ ያለውንም፡ መ—መሐንዲስ አይቸዋለሁ። ከዚህ ጋር ግንኙነት ላላችሁ ሁሉ፡ በእርግጥ ምስጋናችን ላቅ ያለ ነው።

9 ስለ ስጦታዎቹ እያንዳንዳችሁን አመሰግናለሁ። ዛሬ ከሰዓት በኋላ፡ ቢሊ፡ በርካታ፡ ስ—ስጦታዎችን፡ ሳጥኖችን፡ ከረሜላዎችንና፡ የመሳሰሉትን አምጥቶልኛል። ከእነርሱም አንዱ ብፁዓን የ—የሚለውን፡ የተራራው ላይ ስብከት፡ ከክርስቶስ ምስል ጋር አብሮ የተሰራበት ነበር። በእውነትም እጅግ ያማረ ነበር። ከልብ አመሰግናለሁ። ስለ ብዙ ነገሮች፡ እንዴት እንደማመሰግናችሁ አላውቅም። ከዚያም፡ እንዲሁም፡ ለአገልግሎቱ ስላደረጋችሁት የገንዘብ ድጋፍና፡ ስፖንሰር—ስለማድረጋችሁ፡ ከሙሉ ልባችን፡ በእውነት እናመሰግናለን። ጌታ እያንዳንዳችሁን፡ አብዝቶ ይባርካችሁ።

10 በቆይታችን ጊዜ ለግል ቃለ መጠይቆች ስትጠይቁ የነበራችሁ፡ ብዙ ሰዎች እንዳላችሁ፡ ቢሊ ነግሮኛል። ብዙዎች ጠይቀዋል እንዲሁም ለጌታ የሚሰጡ ህጻናት ነበሩአቸው። ኦህ፡ ይህን ማድረግ እንዴት እንደምፈልግ!

ነገር ግን፡ እያችሁ፡ በዚህ ጊዜ ስመጣ፡ በጣም አጣዳፊ ነበር። እነዚህን መልእክቶች ለማምጣት ስል፡ ሁልጊዜ፡ በትክክል በመቆም፡ ይህንን ቃል በጸሎት ማጥናት አለብኝ። እያችሁ፡ እነዚህ... ለእኛ እጅግ—ልዩ ናቸው፡ ምክንያቱም ነገሩ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማግኘትና ከዚያም ነገሮቹን መናገር ስለሆነ ነው። ያ ሁሉ አብሮ መገጣጠም አለበት፡ እኔም የትኛውን መክፈት እንዳለብኝ እግዚአብሔርን እጠይቃለሁ።

11 አሁን፡ የጌታ ፈቃድ ቢሆን፡ አመቺ ቀን እንዳገኘን፡ በቅርቡ እንደገና እንመለሳለን። ስለ ፋሲካ በዓል አ—አንድ ሀሳብ አንስቼ፡ ወ—ወይም የሆነ ነገር ተናግሬ ነበር። በዚያው ሰዓት አካባቢ ካሊፎርኒያ ውስጥ ፕሮግራም

ስላለኝ፡ ያንን ባረጋግጥ ይሻላል። ስለዚህ ያ ሀሳቤ ስህተት ሊሆን ይችላል። ዳሩ ግን፡ ወደ ተብርናክል ዳግመኛ ስንመለስ፡ ካርድ እንልክላችኋለን፡ ቤተክርስቲያኒቱንም አሳውቀን፡ ቀ—ቀኑንና ሰ—ሰዓቱን እንነግራችኋለን። ከዚያም፡ ምናልባት በዚያን ጊዜ፡ እንደገና...

12 ለታማሚዎች ለመጸለይ ምንም ጊዜ አልሰጠሁም። ሰዎችን ወደ ፊት አምጥተን የጸለይንበት አንድም አገልግሎት አልነበረንም። ወደ ውጪ እየላክናቸው ነበር። እዚህ ያሉ ወንድሞቻችን እየሰበኩ ነበር፡ ወንድም ሊ ቬይልና ወንድም... እነዚህ ሌሎች ወንድሞች ሲሰብኩ፡ ለታማሚዎች ሲጸልዩ፡ የውሃ ጥምቀት ሲያደርጉ፡ ማለትም፡ ሲያጠምቁ ቆይተዋል፡ እኔ ደግሞ ከቃሉ ጋር ብቻዬን እንድሆን አድርገውኛል። እነዚህን ሰዎች እናመሰግናለን። ጀግንነት የተሞላበት ታላቅ ሰራ ሰርተዋል።

13 እዚህ ላገኛቸው የምፈልጋቸው እጅግ ብዙ ጓደኞች አሉ። ወደታች ስመለከት ጆንንና አርልን አያለሁ። እንዲሁም ከሰራ አስኪያጆች መካከል አንዱ፡ ዶክተር ሊ ቬይል እዚያ አለ። ወንድም ሮይ ቦርደርስ። እነዚያን ሰዎች፡ ምንም እንኳን... እጃቸውን ከመጨበጥ ያለፈ ምንም እንኳን አላደረግሁም። እድሉን አላገኘሁም። ከኬንታኪና በዚህ አካባቢ ያሉትን፡ ወዳጆቼን፡ አገልጋይ ጓደኞቼንም አሰባለሁ፡ እጃቸውን መጨበጥ እንዴት እንደምፈልግ! ወንድም ብሌየርን፡ በቀደም እዚህ አይቸዋለሁ። በ—በጣም ከምወዳቸው፡ በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ ከተገኙት ከእነዚያ ሰዎች መካከል ብዙዎቹን፡ እጃቸውን እንኳን ጨብጬ አላውቅም። እ—እየሞከርኩ ነው... ያንን ማድረግ ስላልፈለግኩ አይደለም፡ ነገር ግን ጊዜ ስላጣሁና፡ በችኮላ ውስጥ ስለነበርኩ ነው።

14 ህጻናትን ለጌታ መስጠት፡ በእርግጥም መደረግ አለበት። የገዛ ልጄ፡ ትንሹ የልጅ ልጄ በዚህ አገልግሎት ላይ ለጌታ መስጠት ነበረበት። ጊዜ ስላላገኘሁ አላደረግኩትም፥ ትንሹን ዴቪድ። አሁን ለሁለተኛ ጊዜ፡ አያት ሆኛለሁ። ስለዚህ፡ ያንን ምርኩዝ የሰጠኝ፡ ሚስተር ሜይ፡ ዛሬ ማታ እዚህ ካለ፡ በቅርቡ የምጠቀምበት ይመስለኛል።

15 ስለዚህም፡ ለቢሊ እንዲህ አልኩት፡ "መጽሐፍ ቅዱስ 'ብዙ ተባዙ፡ ምድርንም ሙሏት' ብሏል፡ ነገር ግን ሙሉ ሸክሙ ለአንተ ብቻ አልተሰጠም" አልኩት። እነዚህ የልጅ ልጆች በፍጥነት እየመጡ ነው።

ስለዚህም፡ አስታውሱ፡ በመጀመሪያ ደረጃ፡ ምራቴ-መካን-ነበረች። ምንም ልጅ መውለድ አትችልም ነበር። አንድ ቀን፡ ከአንድ ሰብሰባ ሰወጣ፡ ጌታ አናገረኝና እንዲህም አለ፡ "ሎይስ ሆይ፡ ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ። ጌታ ባርኮሻል። የሴት ሕመምሽ ተወግዷልና።" ከዘጠኝ ወራት በኋላ፡ ህጻን ፖል ተወለደ።

16 ይህ ልጅ ወደዚህ ዓለም ከመምጣቱ ከሁለት ወራት በፊት፡ አንድ ቀን ጠዋት ቁርሰ ለመብላት፡ በማዕድ፡ ተቀምጬ ሳለሁ፡ ሎይስና ቢሊ ከማዕዱ ፊት ለፊቴ ተቀምጠው ነበር። ሎይስም በፒንክ... ወይም በሰማያዊ ብርድ ልብሰ የተጠቀለለውን ትንሽ ህፃን ስትመግብ አየሁ። ቢሊ ደግሞ ጥግ ላይ ተቀምጦ፡ ትንሹን ፖልን ይመግብ ነበር። እኔም፡ "ቢሊ፡ አሁን ራእይ አየሁ። ሎይስ በሰማያዊ ብርድ ልብሰ የተጠቀለለ ህፃን ስትመግብ ነበር" አልኩት።

እርሱም፡ “የአደን ጉዞዬን ውሃ በላው ማለት ነው። ያ ደግሞ ልክ ከዘጠኝ ወራት በኋላ የሚሆን ነው” አለ።

ከአስራ አንድ ወራት በኋላ፡ ትንሹ ዴቪድ ተወለደ። እስካሁን ድረስም ለጌታ ልሰጠው አልቻልኩም፡ እንደገና እስክንመለስም አላደርገውም። ስለዚህ ነገሩ ምን እንደሆነ አያችሁ።

17 ሰዎችንና ህብረታቸውን እንዴት እንደምወድ! ሆኖም ወንድሞቻችን ለታማሚዎች ሲጸልዩ ነበር፡ የተሳካ እንደሆነም አውቃለሁ። አንዱ በሌላው ላይ እጁን በመጫን፡ ሁላችንም በአንድነት፡ በየምሽቱ ለታማሚዎች ጸልየናል፡ በዚህ መንገድ ደግሞ ሁሉንም ያዳርሰዋል። ነገር ግን ምናልባት፡ እግዚአብሔር ቢፈቅድ... ካርዱን የምንልክ ከሆነ፡ በካርዱ ላይ ምልክት አደርጋለሁ። ስንመለስ፡ እንደገና፡ ሁለት ወይም ሦስት ቀናት ያህል ለታማሚዎች ለመጸለይና፡ በዚህ ረገድ የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ብቻ ጊዜን መመደብ እፈልጋለሁ። አሁንም፡ ሰዎችን ስለ እርዳታቸው፡ ዳግመኛ አመሰግናለሁ።

18 አሁን በ—በማለዳው መልእክት ላይ፡ ለአፍታ ያህል፡ ጥቂት ሀሳብ መስጠት እፈልጋለሁ። ምንም ጥርጥር የለውም፡ ሙሉ በሙሉ አልጨረስኩትም፡ ነገር ግን የተረዳችሁት ይመስለኛል። እናንተም እንዳላ... ያንን ማድረግ ለእኔ ምን ማለት እንደነበረ አይገባችሁም።

19 አሁን፡ ይህ ለእናንተ በጣም ቀላል ይመስላችኋል። ነገር ግን፡ እናንተ፡ ምን እያደረጋችሁ እንደሆነ አያችሁ? የሆነ ነገር ለማወጅ፡ የእግዚአብሔርን ስፍራ እየወሰዳችሁ ነው። እኔም ያንን ከማድረጌ በፊት፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ መልስ መምጣት ነበረበት። እርሱም መውረድ ነበረበት፡ ራሱንም በሚታይ ሁኔታ ገልጦ፡ መገለጡን ሰጠ። ስለዚህ፡ አያችሁ፡ ይህ ለቤተክርስቲያን ነው። አስታውሱ፡ “እነዚህ፡ ይህ የተናገርኩት፡ ለቤተክርስቲያን ብቻ ነበር፡” ብዬ ነበር።

20 ስለዚህ ድፍረት እንዲኖራችሁና እንድታውቁ፡ ምንም ሽኮኮ በሌለበት በዚያ ስፍራ ላይ፡ “የት እንደሚሆኑ በል፡ ተናገር” ያለኝ ያው እግዚአብሔር ነበር። በተከታታይም ሦስት ጊዜ ተፈጽሟል። አሁን፡ በዚያው ቃል ምንም በሌለበት ስፍራ አንዳች ነገር መፍጠር ከቻለ፡ ይህ ነገር በፍርድ ቀን እንዴት ይበልጥ የጸና አይሆንም! አያችሁ? ሰዎች እነዚህን ነገሮች ለማየትና፡ ለማወቅ በዚያ ነበሩ። ጳውሎስ፡ በቀደምት ዘመናት እንደተናገረው ነው። ምድሪቱ ስትናወጥ የ—የተሰማቸውና፡ ድምፁን ግን ያልሰሙ፡ ሰዎች ከእርሱ ጋር ነበሩ፡ ነገር ግን የ—የ—የእሳት ዓምዱን አይተዋል።

21 ነገር ግን፡ ይህ ካለቀ በኋላ፡ እውነተኛ ክርስቲያኖች መሆናቸውን የማውቃቸው፡ ባሎችና ሚስቶች፡ ተቃቅፈው ሲያለቅሱ ማየቴ፡ እጅግ ደስ አሰኝቶኛል።

22 ወዳጆች ሆይ፡ አዳምጡ፡ እግዚአብሔር ቃሉን፡ የተነገረውን ቃሉን፡ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ቃሉን በምልክቶችና በማጽደቅ ያጸናዋል። አሁን አስታውሱ፡ መገለጡን የሰጠው በዚያ ደመና ውስጥ የነበረው፡ ብርሃን...

እኔ... ትንሿ ልጄ፡ እዚህ ያለችው ሳራ ስትነግረኝ፡ እነርሱ... እዚያ አሪዞና ውስጥ ያለው ትምህርት ቤት ደመና ወደሌለበት ሰማይ ቀና ብለው ሲመለከቱ፡ ይህን ደመና በዚያ ተራራ ላይ በሚሰጥር፡ ወደ-ላይና-ታች ሲወጣና ሲወርድ

አዩት፡ በውስጡም የሚያብረቀርቅ እሳት ይነድ ነበር። መምህሩ ትምህርቱንና ክፍሉን አቋርጦ፡ ተማሪዎቹን ወደ ውጪ በማውጣት፡ እንዲህ አላቸው፡ “እንዲህ ዓይነት ነገር አይታችሁ ታውቃላችሁ? እዚያ ያለውን ሁኔታ ተመልከቱ” አላቸው።

አስታውሱ፡ በዓለቱ ላይ የነበረው ያው የሚያብረቀርቅ ብርሃን ነው። ስለዚህ፡ “**ይህን** እንዲያደርጉ ንገራቸው” ያለው፡ ያው እግዚአብሔር፡ ያው መገለጥ ነው። ዛሬ ጠዋት የነገርኳችሁ ይህንኑ ነው፡ ስለዚህ ይሄውና።

23 ምናልባት ጥሩ ጓደኛዬ፡ ወንድም ሮይ ሮበርሰን፡ ቱክሰን ሆኖ እየሰማኝ ከሆነ ልጠይቀው። ሮይ፡ በቀደም፡ ተራራው ላይ ቆመን ሳለን ያየኸውን ራእይ፡ ታስታውሳለህ? ወደ እኔ መጥተህ፡ ያ ደመናውም ከላይ ሆኖ? ቁልቁል እየወረደ፡ እርሱ ምን እንደነገረህ ታውቃለህ፥ እኔም በቀደም በዚያ ቤት ውስጥ፡ አልነገርኩህም? ሮይ፡ ያ ነው በቃ። ልጄ ሆይ፡ ከእንግዲህ ወዲህ አትጨነቅ። አብቅቷል።

24 ይህ ምን ማለት እንደሆነ ሊገባህ አይችልም! ጸጋ ነው። እሱ ይወድሃል። አንተም ትወደዋለህ፡ በቀሪው ዘመንህ በትህትና አገልግለውና አምልከው። ደስተኛም ሁን፡ እንደሆንከው ሆነህ መኖርህን ቀጥል። ደስተኛ ከሆንክ፡ በዚያው መንገድ ቀጥል። እንደዚያ ዓይነት መጥፎ ነገር ዳግመኛ፡ መቼም አታድርግ። ብቻ ወደ ፊት ቀጥል። የእግዚአብሔር ጸጋ ነው።

25 አሁንም ወደ ቃሉ ከመግባታችን በፊት እንደገና መጸለይ እፈልጋለሁ። ስንቶቻችሁ ትጸልዩልኛላችሁን? ከአንዱ ስብሰባ ወደ ሌላው ስብሰባ እየሄድኩ ነው። ትጸልያላችሁን?

ታውቃላችሁ፡ ወደ ቃሉ ከመሄዳችን በፊት፡ ሁላችንም በአንድነት፡ አንዲት አጭር መዝሙር ብንዘምር ደስ ይለኛል። ብቻ... እግዚአብሔርን እንድናውቅ... ጥቂት ራሳችንን ለመሰጠት ያህል እንዘምር። **እርሱ ያስብላችኋል፡** የምትለውን ይህችን አጭር መዝሙር ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? “በፀሐይ ብርሃንም ሆነ በሐዘንም ውስጥ፡ እርሱ ያስብላችኋል።”

26 ትንሿ እመቤት ወደ ፒያኖው እየወጣች ነው። እውነቱን ለመናገር፡ ይህችን ትንሿን እመቤት ጭምር፡ ማመስገን እፈልጋለሁ። ማን እንደነበረች እንኳን አላውቅም ነበር። እዚህ ካሉት ዲያቆናት የአንዱ ልጅ ናት። በእርግጥም... የወንድም ዊለር ትንሽ ልጅ ናት። አሁን አድጋለች። በቅርቡ፡ ጉልበቴ ላይ ትቀመጥ የነበረች ሚጢጢዬ ልጅ ነበረች፡ አሁን ግን ወጣት ሴት ሆናለች። ስለዚህ ስጦታዋን በሙዚቃ ስላዋለችና፡ አሁን ደግሞ እጅግ በሚጣፍጥ ሁኔታ ስለምትጫወት በእውነት አመሰግናታለሁ። እህቴ፡ ኮርዱን ትሰጪናለሽ? አሁን ሁላችንም በአንድነት።

> እሱ ስለ እናንተ ያስባል፡
> እሱ ስለ እናንተ ያስባል፥
> በጸሐይም ሆነ በጥላ፡
> እሱ ስለ እናንተ ያስባል።

ወደዳችሁት? በድጋሚ እንዘምረው፡ ሁላችሁም በአንድነት።

እሱ ስለ እናንተ ያስባል፡
እሱ ስለ እናንተ ያስባል፥
በጸሐይም ሆነ በጥላ፡
እሱ ስለ እናንተ ያስባል።

ወንድም ዳውች፡ ለአንተም፡ እንዲሁ ያስብልሃል፡ ወንድሜ። ትወደዋለህን?

አሁን እንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

27 ውድ ቸር አምላክ ሆይ፡ ለህዝቡ የምናገራቸው ጥቂት ነገሮች የያዙትን እነዚህን አጫጭር ማስታወሻዎች ይዤ፡ ዳግመኛ ወደ ጠዋቱ መልእክት እመለሳለሁ፡ ምክንያቱም ህዝቡ ሊሰማ የመጣው ያንን ነውና። አምላክ ሆይ፡ ህዝቡ እግዚአብሔር እንደሚወዳቸውና እንደሚያስብላቸው እንዲያዩ እንድታደርግ ዘንድ፡ እጸልያለሁ። ያንንም የሰጠሁት እኔ አይደለሁም፡ ጌታ ሆይ፡ እውነት መሆኑ ጸንቷል። ስለዚህ ውድ አምላክ ሆይ፡ ፍቅርህ ዘወትር በህዝቡ መካከል እንዲኖር፡ እጸልያለሁ። ዛሬ ማታ፡ ከዚህ ስብሰባ በኋላ ተለያይተን ወደየቤታችን መሄዳችን፡ በተወሰነ መልኩ፡ ስ—ስሜታችንን፡ በጥልቅ ይነካዋል፡ ጌታ ሆይ። እነዚህን ሰዎች እንድትባርካቸው እጸልያለሁ።

28 አሁን በጸሎት፡ ወደ ቃሉ ስንቀርብ፡ ወደ ተጻፈው ቃል ስንቀርብ፡ ይህንን የተጻፈ ቃል ወስደህ ዛሬ ማታ ለእኛ ሕያው እንድታደርግልን እንጠይቅሃለን። ዛሬ ማታ ተለያይተን ወደየቤታችን ለመሄድ ከዚህ ሕንፃ ስንወጣ፡ ከኤማሁስ እንደመጡት ሰዎች፡ ቀኑን ሙሉ ከእርሱ ጋር ተጉዘው ገና እንዳላወቁት ሰዎች እንድንል አድርገን፥ ነገር ግን በዚያች ሌሊት ወደ ክፍል ውስጥ ሲያስገባቸውና በሮቹ ሁሉ ሲዘጉ፡ ከመስቀሉ በፊት ያደረገውን ዓይነት ነገር አደረገ። በዚህም፡ ዳግመኛ እንደተነሳ አወቁ።

ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታም እንደገና አድርገው። በሮቹ ተዘግተው፡ ይህ ትንሽዬ መንጋህ እዚህ ተቀምጦ፡ እየጠበቀ ሳለ፡ ይህ ይሁንልን። እንዲሁም፡ አባት ሆይ፡ ወደየቤታችን ስንሄድ፡ እንደ እነርሱ እንዲህ እንላለን፡ "በመንገድ ሲያነጋግረን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን!" ጌታ ሆይ፡ ራሳችንንና፡ ሁሉንም ነገር፡ በእጅህ አደራ እንሰጣለን። መልካም መስሎ የታየህን በእኛ ላይ አድርግ። በኢየሱስ ስም። አሜን።

29 አሁን በፍጥነት፡ ቀጥታ ወደ አገልግሎቱ እንግባ። ፈቃዳችሁ ከሆነ፡ ዕብራውያን መጽሐፍ፡ አብራችሁኝ ግለጡና፡ በመልእክቱ ላይ ወዳለው ሌላ መገለጥ እንመለከታለን። የጌታ ፈቃድ ቢሆን፡ ዛሬ ማታ ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ እንናገራለን። ከዚያም የዕብራውያን 7፡1 እስከ 3 ያሉትን የመጀመሪያዎቹን ሦስት ቁጥሮች እያነበብን፡ በዚህ ላይ ማብራሪያ እንሰጣለን። ጌታ ምን እንደሚያደርግ አናውቅም፥ አናውቅም። የምናደርገው ብቸኛው ነገር ማመን፡ መመልከትና፡ መጸለይ ብቻ ነው። ልክ ነው? እንዲሁም "እግዚአብሔርን ለሚወዱት ነገርን ሁሉ ለበጎ እንዲያደርግ" ማመን ነው፡ ምክንያቱም ተስፋ ሰጥቷልና።

**የሳሌም ንጉሥና፡ የልዑል እግዚአብሔር ካህን የሆነ፡ ይህ መልከ ጼዴቅ፡ አብርሃም ነገሥታትን ገድሎ ሲመለስ ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ፡ ባረከው፥**

**ለእርሱም ደግሞ አብርሃም ከሁሉ አሰራትን አካፈለው፥ የሰሙም ትርጓሜ በመጀመሪያ የጽድቅ ንጉሥ ነው፥ ኋላም ደግሞ የሳሌም ንጉሥ፥ ማለት፥ የሰላም ንጉሥ ነው፥**

ትንሽ ወደፊት እናንብብ።

**አባትና፡ እናት፡ የትውልድም ቍጥር የሉትም፡... ለዘመኑም ጥንት፡** ወይም **ለህይወቱም ፍጻሜ የለውም፥ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ፥ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል።**

30 ይህን ታላቅ አካል አሰቡ፡ ይህ ሰው ምን ያህል ታላቅ መሆን አለበት! አሁንም፡ ጥያቄው፡ "ይህ ሰው ማን ነው? " የሥነ መለኮት ምሁራን የተለያዩ ሀሳቦች ነበሯቸው። ነገር ግን ለእኛ ምስጢር የነበረው ምስጢራዊው መጽሐፍ፡ ሰባቱ ማኅተሞች ከተከፈቱ ጀምሮ... በራእይ 10፥1-7 መሠረት፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፉትና፡ በተሐድሶ አራማጆች ዘመን ሁሉ ተሰውረው የነበሩት ምስጢራት ሁሉ፡ በመጨረሻው የቤተክርስቲያን ዘመን መልአክ በኩል ወደ ብርሃን ሊወጡ ይገባቸዋል። ይህ ልክ እንደሆነ ሰንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? ልክ ነው፡ ሊመጣ ይገባዋል። የምስጢራዊው መጽሐፍ ምስጢራት በሙሉ ለዚያ ዘመን የሎዶቅያ መልእክተኛ ሊገለጡ ይገባዋል።

31 ስለዚህ አካልና ስለዚህ ርዕሰ ጉዳይ ብዙ ክርክር ሰላለ፡ ይህ ማን እንደሆነ ለማወቅ፡ ወደ ጉዳዩ ጠለቅ ብለን መግባት ተገቢ ይመስለኛል። አሁን፡ ስለ እርሱ የተለያዩ አስተሳሰቦች አሉ።

ከአስተሳሰቦቹ አንዱ፡ "እርሱ ዝም ብሎ ተረት ነው። በእርግጥም አካል አልነበረም፡" ይላል።

ሌሎቹ ደግሞ፡ "ክህነት ነበር። የመልከ ጼዴቅ ክህነት ነበር፡" ይላሉ። ክህነት ነው ሰለሚሉ፡ ከሌላው ይልቅ ወደዚህኛው የሚያደሉት፡ ይህኛው ይበልጥ ሊሆን የሚችል ስለመሰላቸው ነው።

ይሁን እንጂ ይህ ሊሆን አይችልም፡ ምክንያቱም በ4ኛው ቁጥር ላይ እርሱ አካል፡ "ሰው" እንደሆነ ይናገራልና። ስለዚህ፡ አካል ለመሆን፡ ስብዕና ሊኖረው ይገባል፡ ይኸውም "ሰው" መሆን አለበት። ሥርዓተ ማዕረግ አይደለም፥ ነገር ግን አካል ነው! ስለዚህ እርሱ የክህነት ሥርዓት ብቻ አልነበረም፡ ወይም ተረት አልነበረም። እርሱ አካል ነበር።

32 ይህ አካል ደግሞ ዘላለማዊ ነው። ካስተዋላችሁ፡ "አባት አልነበረውም። እናት አልነበረችውም። የተጀመረበት ጊዜ አልነበረውም። የሚያበቃበትም ጊዜ አልነበረውም።" ይህ ማንነት ዛሬ ማታም አሁንም ሕያው ነው፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ እዚህ ላይ፡ እንዲህ፡ "አባት እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም፡ ለዘመኑም ጅማሬ፡ ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም፡" ብሏልና። ስለዚህ ዘላለማዊ አካል መሆን አለበት። ልክ ነው? ዘላለማዊ አካል! ስለዚህ ይህ ሊሆን የሚችለው አንድ አካል ብቻ ነው፡ እርሱም እግዚአብሔር ነው፡ ምክንያቱም ዘላለማዊ የሆነው እርሱ ብቻ ነውና። እግዚአብሔር!

33 አሁን፡ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 6፥15ና 16 ላይ፡ ጊዜ ሲኖራችሁ፡ እንድታነቡት እፈልጋለሁ።

አሁን፡ የምሞግትበት ነገር፡ ቢኖር፡ እርሱ እግዚአብሔር እንደነበረ ነው፡ ምክንያቱም የማይሞት አካል ሊሆን የሚችለው እርሱ ብቻ ነውና። አሁንም፡ እግዚአብሔር ራሱን ወደ አካል ለወጠ፥ እርሱም ያ ነበር፡ "አባት የሌለው፡ እናት የሌለችው፡ ለሕይወቱ መጀመሪያ፡ ለቀኖቹም ፍጻሜ የሌለው" ነበር።

34 አሁን "በምልአተ መለኮት ውስጥ ሦስት ሰብዕናዎች አሉ" ብለው የሚያስተምሩ፡ ብዙ ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን። ስለዚህ፡ አካል ሳትሆኑ ሰብዕና ሊኖራችሁ አይችልም። ሰብዕና እንዲኖር አንድ አካል ያስፈልጋል።

ከጥቂት ሳምንታት በፊት፡ አንድ የባፕቲስት አገልጋይ፡ ወደ ቤቴ፡ መጣና፡ እንዲህ አለ፡ "ጊዜ ስታገኝ ስለ መለኮት ላርምህ እፈልጋለሁ" አለኝ። ይልቁንም፡ በስልክ ነው የደወለልኝ።

35 እኔም፡ "ትክክል መሆን ስለምፈልግ፡ አሁን ጊዜ አለኝ፡ ስለዚህ ሌላውን ነገር ሁሉ ወደ ጎን ትተን፡ ይህንን እናድርግ" አልኩት።

እርሱም መጥቶ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ እግዚአብሔር አንድ ብቻ እንደሆነ ታስተምራለህ፡" አለኝ።

እኔም፡ "አዎን፡ ጌታዬ" አልኩት።

እርሱም፡ "መልካም፡" እንዲህ አለ፡ "እኔ አንድ እግዚአብሔር እንዳለ አምናለሁ፡ ነገር ግን አንድ እግዚአብሔር በሦስት አካላት ውስጥ ነው" አለ።

እኔም፡ "ጌታዬ፡ እስቲ ያንን ደግመህ ንገረኝ" አልኩት።

እርሱም፡ "አንድ እግዚአብሔር፡ በሦስት አካላት" አለ።

36 "የት ነው የተማርከው፡" አልኩት? አያችሁ? እርሱም የ—የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ውስጥ እንደተማረ ነገረኝ። እኔም እንዲህ አልኩት፡ "ያንን ማመን እችላለሁ። ሰብዕና ሳይኖርህ አካል ልትሆን አትችልም። ሰብዕና ካለህ ደግሞ፡ ለራስህ አንድ ሰብዕና አለህ ማለት ነው። የተለያየህ፡ ራስህን የቻላህ ግለሰብ ነህ" አልኩት።

እርሱም፡ "መልካም፡ የሥነ መለኮት ምሁራን እንኳን ይህንን ሊያብራሩት አይችሉም" አለኝ።

"በመገለጥ ነው፡" አልኩት።

እርሱም፡ "መገለጥን መቀበል አልችልም" አለኝ።

37 እኔም፡ "እንግዲያውስ እግዚአብሔር ወደ አንተ የሚደርስበት ምንም መንገድ የለም፡ ምክንያቱም፡ 'ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ተሰውሯል፡ ለሕፃናት ግን ተገልጧል፡' ተገልጧል፡ መገለጥ ነው፡ 'ይቀበሉትና ይማሩት ዘንድ ለሕፃናት ተገልጧል፡' አልኩት።" በመቀጠልም፡ "እግዚአብሔር ወደ አንተ የሚመጣበት ምንም መንገድ ሊኖር አይችልም፥ ራስህን ከእርሱ ዘግተሃል" አልኩት።

መላው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው። መላዋ ቤተክርስቲያን የተገነባችው በእግዚአብሔር መገለጥ ላይ ነው። እግዚአብሔርን ማወቅ የሚቻልበት ሌላ መንገድ የለም፡ በመገለጥ ብቻ ነው። "ወልድም ሊገለጥለት ከሚፈቅድ በቀር።" መገለጥ፥ ሁሉም ነገር መገለጥ ነው። ስለዚህ፡ ለመቀበ-... መገለጥን አለመቀበል፡ እንደዛ ከሆነ

አንተ ዝም ብለህ ደረቅ ሥነ መለኮት ምሁር ነህ ማለት ነው፡ ምንም ተስፋ የለህም።

38 አሁን፡ አሁን፡ ይህ አካል "አባት የሌለው፡ እናት የሌለችው፡ ለዘመኑም ጅማሬ ወይም ለሕይወቱም ፍጻሜ የሌለው" እንደሆነ እናውቃለን። እርሱም እግዚአብሔር ነበር፡ **ኤን ሞርፌ።**

አሁን፡ ቃ—ቃሉ የመጣው ከግሪክ፡ ቃል ሲሆን፡ "መለወጥ፡" ማለት ነው፡ ጥቅም ላይ የዋለውም፡ ራሱን መለወጥ፡ **ኤን ሞርፌ**፡ ከአንድ አካል ወደ... አንድ አካል፡ በዚያ ያለው የግሪክ ቃል፡ **ኤን ሞርፌ**፡ ማለት... ከመድረክ ትወና የተወሰደ ነው፡ ይኸውም አንድ ሰው ሌላ ገጸ ባህሪ ሆኖ ለመታየት፡ ጭንብሉን ሲቀይር ማለት ነው።

39 ልክ በ—በትምህርት ቤት ውስጥ፡ በቅርብ ጊዜ ይመስለኛል፡ ይመስለኛል፡ ርብቃ፡ ልትመረቅ ስትል፡ ከሼክስፒር ተውኔቶች አንዱን አቅርበው ነበር። አንድ ወጣት ልብሱን ብዙ ጊዜ መቀየር ነበረበት፡ ምክንያቱም ሁለት ወይም ሦስት የተለያዩ ገጸ ባህሪዎችን ይጫወት ስለነበር ነው፥ ነገር ግን፡ ያው አንድ ሰው ነው። አንድ ጊዜ፡ ወጥቶ፡ ተንኮለኛ ይሆናል፥ ቀጥሎ ሲወጣ፡ ደግሞ ሌላ ገጸ ባህሪ ይሆናል። አሁንም **ኤን ሞርፌ** የሚለው፡ የግሪክ ቃል፡ "ጭንብሉን ቀየረ" ማለት ነው።

40 እግዚአብሔርም ያደረገው ያንን ነው። ሁልጊዜም ያው አንድ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር በአብ፡ በ—በመንፈስ፡ በዐሳቱ ዓምድ መልክ። ያው እግዚአብሔር ሥጋ ሆነ በእኛም ዘንድ አደረ፡ **ኤን ሞርፌ፡** ሊታይ በሚችልበት ሁኔታም መጣ። አሁንም ያው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው። አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ... ሦስት አማልክት አይደሉም፥ የአንዱ እግዚአብሔር ሦስት የሥራ ድርሻዎች፡ ሦስት ተግባራት ናቸው እንጂ።

41 መጽሐፍ ቅዱስ፡ "አንድ እግዚአብሔር አለ" ይላል እንጂ፡ ሦስት አይልም። ዳሩ ግን ለዚህም ነው እነርሱ... ሦስት አማልክት እያሏችሁ ይህንን ልታስተካክሉት አትችሉም። ይህንን ለአይሁዳዊ መቼም ልታሳምኑት አትችሉም። ይህንን እነግራችኋለሁ። በሚገባ የሚያውቅ ሰው፡ አንድ እግዚአብሔር ብቻ እንዳለ ያውቃል።

42 አስተውሉ፡ ልክ እንደ ቀራጺ፡ ከላይ በ—በጭንብል፡ ይሸፍነዋል። እግዚአብሔርም በዚህ ዘመን ያደረገው ያንን ነው። ተሰውሮ ቆይቷል። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ተሰውረው የቆዩ ሲሆን፡ በዚህ ዘመን ደግሞ ሊገለጡ ይገባቸዋል። አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ በኋለኛው ዘመን እንደሚገለጡ ይናገራል። ይህም አንድ ቀራጺ የ—የሰራውን ሰራ ጭንብሉን ገፎ እስኪያሳየውና ይኸውላችሁ እስኪል ድረስ ሙሉ በሙሉ ሸፍኖ እንደሚያቆየው ማለት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስም እንዲሁ ነበር። ተሸፍኖ የቆየ የእግዚአብሔር ሰራ ነበር። ከዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ፡ እርሱና ሰባት እጥፍ የሆነው ምስጢሩ ተሰውሮ ቆይቷል። እግዚአብሔርም በዚህ ዘመን፡ በዚህ በሎዶቅያ ቤተክርስቲያን ዘመን፡ ከሁሉም ላይ ጭንብሉን ገፎ እንደሚያነሳውና እኛም ልናየው እንደምንችል ተስፋ ሰጥቷል። እንዴት ያለ ክቡር ነገር ነው!

43 እግዚአብሔር፡ **ኤን ሞርፌ፡** በእሳት ዓምድ ውስጥ ተጋርዶ ነበር። እግዚአብሔር፡ **ኤን ሞርፌ፡** ኢየሱስ በሚባል ሰው ውስጥ። እግዚአብሔር፡ **ኤን**

**ሞርፌ፡** በቤተክርስቲያኑ ውስጥ። እግዚአብሔር ከእኛ በላይ፡ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር፥ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ፥ የእግዚአብሔር ራሱን ዝቅ በማድረግ።

እዚያ ላይ፡ ቅዱስ ሆኖ፡ ማንም ሊነካው አልቻለም፥ ተራራው ላይ ወረደ፡ እንስሳ እንኳን ተራራውን ቢነካ፡ መሞት ነበረበት።

ከዚያም እግዚአብሔር ወረደና ድንኳኑን ቀየረ፡ ወርዶም ከእኛ ጋር ኖረ፡ ከእኛም አንዱ ሆነ። መጽሐፍ ቅዱስም፡ "እኛም ዳሰስነው" ይላል። 1ኛ ጢሞቴዎስ 3፥16፡ "እግዚአብሔርን የመምሰል ምስጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፥ እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠ፡ በእጅም ተዳሰሰ" ይላል። እግዚአብሔር ስጋ በላ። እግዚአብሔር ውሃ ጠጣ። እግዚአብሔር ተኛ። እግዚአብሔር አለቀሰ። ከእኛ አንዱ ነበር። ውብ ነው፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምሳሌው ተቀምጧል!

ያ እግዚአብሔር ከእኛ በላይ፥ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር፥ አሁን ደግሞ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ነው፡ እርሱም መንፈስ ቅዱስ ነው። ሦስተኛ አካል አይደለም፥ ያው አንድ አካል ነው!

44 እግዚአብሔር፡ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ፡ ለኅብረት መኖር እንዲችልና፡ እርሷንም ያነጻ ዘንድ፡ በክርስቶስ ሥጋ ሆኖ ወረደ፡ ሞትንም ሞተ። እግዚአብሔር ኅብረትን ይወዳል። በመጀመሪያ ጊዜ ሰውን የፈጠረው ለዚሁ ነበር፡ ይኸውም ለህብረት ነበር፥ እግዚአብሔር ከኪሩቤሎች ጋር፡ ብቻውን ይኖር ነበርና።

45 አሁንም አስተውሉ፡ ሰውን ፈጠረ፡ ሰውም ወደቀ። እግዚአብሔር መመለክን ስለሚወድ፡ ወርዶ ሰውን ተበዠ። **አምላክ** የሚለው ቃል ራሱ "የሚመለክ አካል" ማለት ነው።

በእኛም መካከል፡ እንደ እሳቱ ዓምድ የሚመጣው፡ ልባችንን እንደሚለውጥ ሆኖ የሚመጣው ይህ፡ "ብርሃን ይሁን" ያለና፡ ብርሃንም የሆነለት፡ ያው እግዚአብሔር ነው። እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው።

46 አሁን፡ ዛሬ ጠዋት እንደተናገርኩት፡ በመጀመሪያ እግዚአብሔር፡ ከባህሪያቱ ጋር ብቻውን ይኖር ነበር። እነርሱም ሀሳቦቹ ናቸው። ምንም አልነበረም፡ እግዚአብሔር ብቻውን ነበር፡ ዳሩ ግን ሀሳቦች ነበሩት።

ልክ አንድ ታላቅ ንድፍ አውጪ ተቀምጦ፡ ሊገነባው ያሰበውን ነገር፡ በአእምሮው ውስጥ፡ እ—እንደሚስለው ማለት ነው። አሁን፡ መፍጠር፡ እርሱ መፍጠር አይችልም። የተፈጠረውን ነገር ወስዶ በሌላ መልክ ሊሰራው ይችላል፥ ምክንያቱም እግዚአብሔር ብቸኛው መንገድ... መፍጠር የሚችለው አንድ እርሱ ብቻ ነውና። ነገር ግን ምን ሊያደርግ እንዳሰበ በአእምሮው ውስጥ ይስለዋል፡ ያም ሀሳቡ ነው፡ ያም ፍላጎቱ ነው። አሁን እርሱ ሀሳብ ነው፡ ከዚያም ይናገረዋል፡ በዚያን ጊዜ ቃል ይሆናል።

47 ቃ—ቃል ማለት ሀሳብ ነው፡ ሲገለጽ ደግሞ፡ ቃል ይሆናል። የተገለጠ ሀሳብ ቃል ነው፡ ዳሩ ግን መጀመሪያ ሀሳብ መሆን አለበት። ስለዚህ፡ እርሱ የእግዚአብሔር ባህርይ ነው፥ ከዚያም ሀሳብ ይሆናል፡ ቀጥሎም ቃል ይሆናል።

48 አስተውሉ። ዛሬ ማታ፡ የዘላለም ሕይወት፡ ያላችሁ ሰዎች፡ መልአክ፡ ኮከብ፡ ኪሩቤል፡ ወይም ሌላ ማንኛውም ነገር ከመኖሩ በፊት፡ ከእርሱ ጋርና በእርሱ ውስጥ፡ በሀሳቡ ውስጥ ነበራችሁ። ያ ዘላለማዊ ነው። የዘላለም ሕይወት ካላችሁም፡ ሁልጊዜም ነበራችሁ ማለት ነው። አሁን እዚህ መኖራችሁ ሳይሆን፡ ወሰን የሌለው እግዚአብሔር የሰጣችሁ መልክና ቅርጽ...

49 እርሱ ወሰን የሌለው ካልሆነ፡ እግዚአብሔር አይደለም ማለት ነው። እግዚአብሔር ወሰን የሌለው መሆን አለበት። እኛ ወሰን ያለን ነን፥ እርሱ ግን ወሰን የሌለው ነው። እንዲሁም እርሱ በሁሉ ሰፍራ የሚገኝ፡ ሁሉን አዋቂና፡ ሁሉን ቻይ ነበር። እንዲህ ካልሆነ፡ እርሱ እግዚአብሔር ሊሆን አይችልም። በሁሉ ሰፍራ የሚገኝ በመሆኑ፡ ሁሉን ነገር፡ ሁሉንም ሰፍራዎች ያውቃል። ሁሉን አዋቂነቱ በሁሉ ሰፍራ የሚገኝ ያደርገዋል። እርሱ ህልውና ነው፥ እንደ ንፋስ አይደለም። እርሱ የሚኖር ነው፥ በማደሪያ ውስጥ ይኖራል። ዳሩ ግን ሁሉን አዋቂ መሆኑ፡ ሁሉንም ነገር ማወቁ፡ በሁሉ ሰፍራ የሚገኝ ያደርገዋል፡ ምክንያቱም እየሆነ ያለውን ነገር ሁሉ ያውቃልና።

አንዲት ቁንጫ እንኳን እርሱ ሳያውቅ ዓይኗን ልታርገበግብ አትችልም። ዓለም ከመፈጠሩ በፊት፡ ስንት ጊዜ ዓይኗን እንደምታርገበግብና፡ ምን ያህል ስብ በውስጧ እንዳለ፡ ያውቅ ነበር። ያ ነው ወሰን የሌለው መሆን። በአእምሯችን ልንረዳው አንችልም፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ማለት ያ ነው። ወሰን የሌለው፡ እግዚአብሔር!

50 አስታውሱ፡ እናንተ፡ ዓይኖቻችሁ፡ ቁመናችሁ፡ ማንኛችሁም ብትሆኑ፡ በመጀመሪያ በእርሱ ሀሳብ ውስጥ ነበራችሁ። እናንተም መገለጫ፡ ቃል ብቻ ናችሁ። እርሱ ካሰበው በኋላ፡ ተናገረው፡ እናንተም ይኸው እዚህ አላችሁ። እንዲህ ካልሆነ፡ በእርሱ ሀሳብ ውስጥ ካልነበራችሁ፡ በዚህ ልትገኙ የምትችሉበት ምንም መንገድ የለም፡ የዘላለምን ሕይወት የሚሰጠው እርሱ ብቻ ነውና።

51 መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እንዳነበብነው ታስታውሳላችሁን? "ለወደደ፡ ወይም ለሮጠ አይደለም፡ ከእግዚአብሔር ነው እንጂ!" አስቀድሞ መወሰኑም ጸንቶ እንዲቆም፡ ከዘመናት በፊት፡ ሊመርጥ ችሏል። ማን... እግዚአብሔር በምርጫው ሉዓላዊ ነው። ይህን ታውቁ ነበርን? እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው።

ዓለምን የሚሰራበትን የተሻለ መንገድ ሊነግረው በዚያ ጊዜ ማን ነበረ? ስራውን በተሳሳተ መንገድ እየሰራ እንደሆነ ሊነግረው የሚደፍር ማን ነበረ?

ቃ—ቃሉ፡ ራሱ እንኳን፡ እጅግ ሉዓላዊ ነው። መገለጥ እንኳን ሉዓላዊ ነው። "ሊገልጥለት ለሚፈቅደው ይገልጣል።" መገለጡ፡ ራሱ፡ በእግዚአብሔር ውስጥ ሉዓላዊ ነው። ሰዎች ምን እያደረጉ እንዳሉ ሳያውቁ፡ ነገሮችን የሚወግሩት፡ በነገሮች ላይ የሚዘልሉትና፡ ነገሮችን የሚመቱትም ለዚህ ነው። እግዚአብሔር በሰራዎቹ ሉዓላዊ ነው።

52 አሁን በመጀመሪያ፡ እርሱን ከባህሪያቱ ጋር እናገኘዋለን። አሁንም፡ በዚያን ጊዜ፡ ከእርሱ ጋር ነበራችሁ። የሕይወት መጽሐፍ ወደ እይታ የሚመጣው በዚያን ጊዜ ነው።

አሁን፡ እዚህ ራእይ ምዕራፍ 13፡ ቁጥር 8 ላይ፡ ይህም፡ በዚህ በመጨረሻዎቹ ቀናት፡ "በምድር ላይ የሚወጣው አውሬ፡" "ዓለም ከመፈጠሩ

በፊት ጀምሮ በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ስሞቻቸው ያልተጻፉትን በምድር ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ ያስታል" ብለን እናነባለን።

53 እስቲ አስቡት! ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት፡ ወደ ምድር ከመምጣቱ አራት ሺህ ዓመታት በፊት፡ እንዲሁም እናንተ ወደ ምድር ከመምጣታችሁ ከበርካታ ሺህ ዓመታት በፊት፡ ኢየሱስ፡ በእግዚአብሔር አእምሮ ውስጥ፡ ለዓለም ኃጢአት ሞቷል፡ የሕይወት መጽሐፍም ተዘጋጅቷል፡ እንዲሁም ዓለም ከመፈጠሩ በፊት፡ ስማችሁ በዚያ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ሰፍሯል። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነው። እያችሁ፡ ስማችሁ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በእግዚአብሔር ታቅዶ በሕይወት መጽሐፍ ላይ ተጽፎ ነበር።

54 በእርሱ ባህርያት ውስጥ በዚያ ነበራችሁ። የሕይወቱ አካል ብቻ ስለሆናችሁ፡ አታስታውሱትም፡ አይ። የእግዚአብሔር ወንድ ልጅ ወይም ሴት ልጅ ስትሆኑ የእግዚአብሔር አካል ትሆናላችሁ።

ልክ የምድራዊ አባታችሁ አካል እንደሆናችሁት ሁሉ! በትክክል። እናንተ... ወንዱ ሄሞግሎቢን፡ ወይም ደሙን ይሸከማል። ያም ወ—ወደ እንቁላሉ ውስጥ ሲገባ፡ ያኔ የአባታችሁ አካል ትሆናላችሁ፥ እናታችሁም ደግሞ፡ የአባታችሁ አካል ናት፥ ስለዚህ ሁላችሁም የአባታችሁ አካል ናችሁ።

ክብር! ይህ የሐይማኖት ተቋምን ሙሉ በሙሉ፡ ወደ ውጭ ያወጣዋል። ኧ-ህ። በእርግጥም ያደርገዋል! እግዚአብሔር፡ በሁሉም ውስጥ፡ ብቸኛው ሰፍራ ነው!

55 አሁን ባህርይውን አስተውሉ። ከዚያም ባህርይው፡ በመጀመሪያ፡ እግዚአብሔር ነበር፥ ሀሳቡ፡ ባህርይው ራሱ፡ ሳይገለጽ በፊት ሁሉም፡ በአንድ ውስጥ ነበር። ከዚያም፡ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ሲገልጸው፡ ያኔ ቃል ሆነ። "ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ።"

56 የሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 ላይ፡ አስተውሉ፡ ይህም፡ "በመጀመሪያ።" ነገር ግን፡ ከዚያ በፊት፡ ዘላለማዊው ነበረ! አስተውሉ፡ "በመጀመሪያ ቃል ነበረ።" ጊዜ ሲጀምር፡ ቃል ነበረ። ነገር ግን ቃል ከመሆኑ በፊት፡ ባህርይ፡ ሀሳብ ነበረ። ከዚያም ተገለጸ፡ ይኸውም መገለጫው የሆነው፡ "ቃል፡" "በመጀመሪያ ነበረ።"

አሁን መልከ ጼዴቅ ወዳለበት እየመጣን ነው። ያ ምስጢራዊው አካል ነው። "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።" "ከዚያም ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ።" አሁን ያንን እዚያው ያዙት፡ አስተውሉ።

57 የ—የእርሱ የመጀመሪያው ማንነት መንፈስ፡ እግዚአብሔር፡ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ፡ ታላቁ ዘላለማዊ አካል ነበረ፡ በትክክል። በሁለተኛ ደረጃ፡ "ቃል፡ አካል" በሚባለው፡ በ **ቲዮፋኒ** ሆኖ፡ ራሱን ወደ ሥጋ መለወጥ ጀመረ። እንግዲህ አብርሃምን ሲያገኘው የነበረበት ሁኔታ ይህ ነበረ፡ እርሱም መልከ ጼዴቅ ተብሎ ተጠራ። እርሱ በቲዮፋኒ መልክ ነበረ። አሁን፡ የጌታ ፈቃድ ቢሆን፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ወደዚያ ደርሰን እናረጋግጠዋለን። እርሱ ቃል ነበረ።

58 ቲዮፋኒ ማለት ልታዩት የማትችሉት ነገር ነው። አሁን ልክ እዚህ ሊኖር ይችላል፡ ነገር ግን ልታዩት አትችሉም።

ይህ ልክ፡ ደህና፡ እንደ ቴሌቪዥን ማለት ነው። ያ በሌላ ዳይመንሽን ውስጥ ነው። ቴሌቪዥን፥ አሁን በዚህ ክፍል ውስጥ ሰዎች እየዘመሩ፡ እያቋረጡ እያለፉ ነው፡ ቀለማትም፡ አሉ። ነገር ግን ዓይን ለአምስቱ የስሜት ሕዋሳት ብቻ የተገዛ ነው... ይልቁንም መላው ማንነታችሁ ለአምስቱ የስሜት ሕዋሳት ብቻ የተገዛ ነው። እናንተም የተገዛችሁት የማየት አቅማችሁ ሊያየው ለተገደበው ነገር ብቻ ነው። ዳሩ ግን በትራንስፎርሜሽን፡ በቴሌቪዥን አማካኝነት ሊታይ የሚችል ሌላ ዓለም አለ።

59 አሁን፡ ቴሌቪዥን ምስልን አይፈጥርም። ቴሌቪዥን የሚያደርገው ምስሉን በሞገድ ውስጥ እንዲያልፍ ማድረግ ብቻ ነው፡ ከዚያም የቴሌቪዥኑ መስታወት ይቀበለዋል። በመጀመሪያ ደረጃ ግን፡ ምስሉ በዚያው አለ። አዳም እዚህ በነበረበት ጊዜ ቴሌቪዥን እዚህ ነበረ። ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ በተቀመጠበት ጊዜ ቴሌቪዥን እዚህ ነበረ። የናዝሬቱ ኢየሱስ በገሊላ የባህር ዳርቻ በተመላለሰበት ጊዜ ቴሌቪዥን እዚህ ነበረ። ነገር ግን እናንተ አሁን ነው እያገኛችሁት ያላችሁት። በዚያን ዘመን የነበሩ ሰዎች ይህንን አያምኑም ነበረ። እንዲህ ዓይነት ነገር ብትናገሩ ኖሮ እንደ እብድ ትቆጠሩ ነበረ። አሁን ግን እውን ሆኗል።

ክርስቶስም እዚህ መኖሩ፡ የእግዚአብሔር መላእክትም እዚህ መሆናቸው፡ ልክ እንደዚሁ ነው። አንድ ቀንም፡ በሚመጣው ታላቁ የሺህ ዓመት መንግስት ውስጥ፡ ከቴሌቪዥንም ሆነ ከሌላ ከማንኛውም ነገር በላይ እጅግ እውን ይሆናል፡ ምክንያቱም እነርሱ እዚህ አሉና።

60 እርሱም ራሱን በአገልጋዮቹ ውስጥ፡ **ኤን ሞርፌ** ሲያደርግና ራሱን ሲያረጋግጥ አስቀድሞ እንደተናገረው በታላቅ መልኩ ራሱን ይገልጣል።

61 አሁን፡ እዚህ እርሱ በመንፈስ መልክ ነው። ከዚያም የ... የ**ኤን ሞርፌ** መልክ ይዞ ይመጣል። አሁን፡ ለአብርሃም በ**ኤን ሞርፌ**፡ ተገለጠለት። አብርሃም ነገሥታትን ገድሎ ሲመለስ፡ እነሆ መልከ ጼዴቅ መጥቶ፡ አነጋገረው።

62 በቀደም በቱክሰን ጋዜጣ ላይ፡ አንድ ጽሁፍ እያነበብኩ ነበር አ—አንዲት ሴት በመንገድ ላይ፡ በሰዓት አርባ፡ ወይም ሃምሳ ማይል አካባቢ እየነዳች ሳለች፡ ካፖርት የለበሰን አንድ አዛውንት መታች። ጮኸችና መኪናዋን አቆመች። በአየር ላይ ወረወረው። እዚያው ባዶው በረሃ ውስጥ! ልትፈልገው ወደ ኋላ ስትሮጥ፡ እዚያ አልነበረም። ታዲያ ምን አደረገች? ከኋላዋ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች ይህ ሲሆን አይተዋል፡ አዛውንቱ በአየር ላይ ሲበርና፡ ካፖርቱም ሲገለበጥ አይተዋል። ስለዚህ ምን እንደተፈጠረ ለማየት ወደ ኋላ ሮጡ። ሰውንዬውን የትም ሊያገኙት አልቻሉም። ፖሊስ ጠሩ። ፖሊሶች ቦታውን ለመመርመር መጡ፥ ነገር ግን ማንም አልነበረም።

63 እንግዲህ፡ እያንዳንዳቸው፡ "መኪናዋ ተንገጫገጨች፡ ሰውዬውንም መታችው። በአየር ላይ ተወረወረ፡ ሁሉም አይቶታል" ብለው መሰከሩ። የዓይን እማኞች፡ ሁለት ወይም ሦስት መኪና ሙሉ የሆኑ ሰዎች፡ ሲከሰት አይተዋል። በኋላ ሲጣራ፡ ከዛሬ አምስት ዓመት በፊት፡ ካፖርት የለበሰ አንድ አዛውንት፡ ልክ በዚያው ቦታ ተመትቶ ሞቶ ነበር።

ከዚህ ስትወጡ፡ አልሞታችሁም። ኃጢአተኛ እንኳን ብትሆኑ፡ ተመልሳችሁ መጥታችሁ በስጋችሁ ባደረጋችሁት ስራ መጠን፡ ሊፈረድባችሁ ይገባል። "ይህ

ምድራዊ ድንኳን ቢፈርስ፡ የሚጠብቀን ሌላ አለን።" **ኤን ሞርፌ፡** ቃሉ ያ ነው።

64 አሁን፡ እግዚአብሔር፡ በዚህኛው ደረጃ... በኋላ በሥጋ፡ ኢየሱስ በሆነበት፡ የፍጥረቱ ደረጃ ውስጥ ነው። ከምን? ከታላቁ መጀመሪያ፡ ከመንፈስነት ጀምሮ፡ ከዚያም ራሱን ወደ ውጪ በማምጣት፡ ቃል ለመሆን ወረደ። ቃሉ ገና ራሱን አላደረገም፡ በ**ኤን ሞርፌ** መልክ፡ ተነገረ እንጂ፡ በኋላ ግን ለእኛ ለኃጢአተኞች ሁሉ፡ ሞትን ይቀምስ ዘንድ፡ ሟች ሥጋ፡ ኢየሱስ ሆነ።

65 አብርሃም ሲያገኘው፡ እርሱ መልከ ጼዴቅ ነበረ። ሁሉም ባህርያት፡ እያንዳንዱ የአብርሃም ልጅ በመጨረሻው ፍጻሜ ምን እንደሚያደርግ እዚህ ላይ ይገልጠዋል። እያንዳንዱ የእምነት ልጅ ያለምንም ጥርጥር ያኑ ነገር ያደርጋል። ነገር ግን እኛ እንዴት መምጣት እንዳለብን እንድናስተውል እፈልጋለሁ።

66 እንዲሁም፡ በሩትና በ—በቦዔዝ ታሪክ ውስጥ፡ እንደ የቅርብ ዘመድ ቤዛ፡ ሥጋ ሆኖ መምጣት እንዴት እንደነበረበት ሲገለጥ እዚህ እናየዋለን።

67 አሁን እንደምናየው የገዛ መንፈሱ የባሕርይ-ልጆች የሆኑት፡ ከቃል ወደ ተሠራው አካል-ቅርጽ ውስጥ ገና አልገቡም... ነገር ግን... ቲዮፋኒ። **ይህ** አካል ለቃሉ የተገዛ ነው... እንዲሁም የመያዣውን፡ ማለትም የአካሉን መለወጥ በመጠባበቅ ላይ ነው።

68 አሁን፡ በእርሱና በእናንተ መካከል ያለው ልዩነት፡ እንደ ልጅ፥ አያችሁ፡ በመጀመሪያ፡ እርሱ፡ ቃል ነበረ፡ **ኤን ሞርፌ** የሆነው አካል፡ መጥቶም በመልከ ጼዴቅ ማንነት በዚያ ውስጥ ኖረ፡ ከዚያም በኋላ ስለ መልከጼዴቅ ምንም አልሰማንም፡ ምክንያቱም እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ፡ መልከጼዴቅ ካህን ነበር ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ፡ አሁን፡ እናንተ ያንን ደረጃ ዘልላችሁ አልፋችሁታል፡ ምክንያቱም እርሱ በዚያ መልክ ሳለ ሁሉን ነገር ያውቅ ነበረ፡ እናንተ ግን ያንን እስካሁን ማወቅ አልቻላችሁም።

እንደ አዳም፡ እንደ እኔ መጣችሁ፡ ልትፈተኑም፡ ከባህርይነት ወደ ሥጋነት ተለወጣችሁ። ነገር ግን እዚህ ያለው ይህ ሕይወት ሲያበቃ፡ "ይህ ምድራዊ ድንኳን ቢፈርስ፡ ተዘጋጅቶ የሚጠብቀን ሌላ አለን።" የምንሄድበትም ስፍራ ያ ነው፥ ያም ቃሉ ነው። በዚያን ጊዜ ወደ ኋላ መለስ ብለን ያደረግነውን ማየት እንችላለን። አሁን ግን አይገባንም። በጭራሽ ቃል አልሆንንም፥ ልክ የሥጋ-ሰው ሆንን እንጂ፡ ቃል አልሆንንም።

69 ነገር ግን፡ እስቲ ተመልከቱ፡ በመጀመሪያ ሀሳብ ካልነበራችሁ በስተቀር መቼም ቃል ልትሆኑ እንደማትችሉ፡ በግልጽ ያሳያል። ያም የእግዚአብሔርን አስቀድሞ መወሰን ያረጋግጣል። አያችሁ? ሀሳብ ካልሆናችሁ በስተቀር ቃል ልትሆኑ አትችሉም። በመጀመሪያ፡ በሀሳቡ ውስጥ መሆን ነበረባችሁ።

ነገር ግን፡ አያችሁ፡ ፈተናን ለመቋቋም፡ የቲዮፋኒን ደረጃ ዘልላችሁ ማለፍ ነበረባችሁ። በኃጢአት ትፈተኑ ዘንድ፡ በሥጋ ወደዚህ መውረድ ነበረባችሁ። ከዚያም፡ ጸንታችሁ ከቆማችሁ፡ "አብ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፡ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሳዋለሁ።" አያችሁ፡ መጀመሪያ በዚያ መሆን ነበረባችሁ።

70 ከዚያም፡ እያችሁ፡ እርሱ በትክክለኛው መስመር፡ ወደታች መጣ፡ ከባህርይነት ወደ... ዓለም ከመመስረቱ በፊት፡ ስሙ በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ሰፍሮ ነበር። ከዚያም፡ ከዚያ በመነሳት፡ ሊገለጥና፡ ሊሰወር የሚችለው፡ ቃል፡ ቲዮፋኒ ሆነ። በመቀጠልም ሥጋ ሆነና ዳግመኛ ተመልሶ ሄደ፡ ያንኑ አካል በከበረ ሁኔታ አስነሳው።

እናንተ ግን በኃጢአት ትፈተኑ ዘንድ፡ ቲዮፋኒውን አልፋችሁ የሥጋ-ሰው ሆናችሁ። ከዚያም፡ "ይህ ምድራዊ ድንኳን ቢፈርስ፡ ተዘጋጅቶ የሚጠብቀን ሌላ አለን።" ገና እነዚያ አካላት የሉንም።

71 ነገር ግን፡ ተመልከቱ! ይህ ሥጋ የእግዚአብሔርን መንፈስ፡ በውስጣችሁ ያለውን የማይሞተውን ሕይወት ሲቀበል፡ ይህንን ሥጋ ለእግዚአብሔር እንዲገዛ ያደርገዋል። ሃሌሉያ! "ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፥ ኃጢአትንም ሊያደርግ አይችልም።" ሮሜ 8፥1፡ "እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም፥ እንደ መንፈስ እንጂ፡ እንደ ሥጋ አይመላለሱም።" ይኸውና እያችሁ። እያችሁ፡ ያ ሥጋችሁ እንዲገዛ ያደርገዋል።

"ኦህ፡ መጠጣት ማቆም ብቻ ብችል ኖሮ! ይህንን ማድረግ ብቻ ብችል ኖሮ፡" ማለት አያስፈልጋችሁም... ወደ ክርስቶስ ብቻ ግቡ፡ ከዚያም ሁሉም ይጠፋል፡ እያችሁ፡ እያችሁ፡ ምክንያቱም ሥጋችሁ ለመንፈስ የተገዛ ይሆናልና። ከእንግዲህ ለዓለም ነገሮች የተገዛ አይደለም፥ እነርሱ ሞተዋል። ሞተዋል፥ ኃጢአታችሁ በጥምቀት ተቀብሯል፡ እናንተም በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ናችሁ። ሥጋችሁም፡ ለመንፈስ በመገዛት፡ ትክክለኛውን ዓይነት ሕይወት ለመኖር ይጥራል።

72 መንፈስ ቅዱስ አለን እያላችሁ፡ አጫጭር ልብሶችንና የመሳሰሉትን ለብሳችሁ ወደ ውጪ የምትወጡት እናንተ ሴቶች፡ ይህንን እንዴት ልታደርጉ ትችላላችሁ? በውስጣችሁ ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ እንዴት እንዲህ ዓይነቱን ነገር እንድታደርጉ ሊፈቅድላችሁ ይችላል? እንዲህ ሊሆን በፍጹም አይችልም። በእርግጠኝነት፡ ሊሆን አይችልም። እርሱ ርኩስ መንፈስ አይደለም፥ እርሱ ቅዱስ መንፈስ ነው።

73 ከዚያም ለዚያ መንፈስ ስትገዙ፡ መላው ማንነታችሁን ለዚያ መንፈስ እንዲገዛ ያደርገዋል። ያም መንፈስ ከዚህ ከተገለጠው፡ ወይም ሕያው ከሆነው፡ ሃሌሉያ፡ ሕያው ከተደረገው የዘር ቃል በቀር በዓለም ላይ ሌላ ምንም አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስም፡ "**ይህንን** አታድርጉ" ሲል፡ ያ ሥጋ ወዲያውኑ ወደ ቃሉ ዘወር ብሎ ይታዘዛል። ምንም ጥያቄ የለውም።

ይህ ምንድ ነው? የትንሳኤው መያዣ ነው። ይህ አካል ዳግመኛ ይነሳል፡ ምክንያቱም አሁን ተጀምሯልና። በአንድ ወቅት ለኃጢአት፡ ለጭቃና ለመበስበስ የተገዛ ነበር፡ አሁን ግን መያዣውን አግኝቷል፥ ሰማያዊ ሆኗል። አሁን፡ በንጥቀት እንደምትሄዱ የሚያሳየው መያዣ ያ ነው። መያዣው ነው።

74 ታሞ የተኛ፡ እየሞተ ያለ ሰው፡ ከሞት በቀር ምንም ያልቀረው ሰው፥ ሊሆን የሚችለው ያ ብቻ ነው። በካንሰርና በሳንባ ነቀርሳ ተበልተው ያበቁ፡ የሰው ጥላ እስኪመስሉ የከሱ ሰዎችን አይቻለሁ፥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን፡ እነዚያው ሰዎች ሙሉ በሙሉ ጤናማና ብርቱ ሆነው አይቻለሁ። መለኮታዊ ፈውስ

ከሌለ፡ ትንሳኤም የለም፡ ምክንያቱም መለኮታዊ ፈውስ የትንሳኤው መያዣ ነውና። አሜን!

75 የመያዣ ገንዘብ ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ፡ አይደል? ቅድመ ክፍያ ነው። “እርሱ ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፥ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን።” እንዴት ድንቅ እንደሆነ አስተውሉ! እንወደዋለን።

76 አሁን፡ ይህ አካል ለመንፈስ የተገዛ ነው። ገና ወደ ቃል ቅርጽ አልገባንም፡ ነገር ግን አሁንም በሥጋ ቅርጽ ውስጥ ነን፡ ሆኖም ለቃሉ የተገዛን ነን። በሥጋ መሞት ወደዚያ ይወሰደናል።

77 ልክ እንደዚሁ፡ እስቲ ስለ አንድ ትንሽ ህፃን አስቡ። አንዲት ሴት፡ ምንም ያህል ክፉ ብትሆንም፡ ስታረግዝና እናት ለመሆን ስትዘጋጅ ተመልከቷት። አስተውሉ፡ ያ ህፃን ከመወለዱ በፊት፡ ሴትዮዋ ምንም ያህል ጨካኝ ብትሆን ግድ የለኝም፡ እጅግ ደግ ትሆናለች። በድምጿ ውስጥ የሆነ ነገር አለ... አንዲት እናት በህፃኑ አማካኝነት፡ እናት ለመሆን ስትዘጋጅ ማየት፡ እግዚአብሔራዊነትን የተላበሰ ይመስላል። ለምንድን ነው? ያ ትንሽ አካል፡ አሁን፡ ገና ሕያው አልሆነም፡ አያችሁ፡ ሥጋና ጡንቻ ብቻ ነው ያለው። ያ ትንሽ መዝለል፡ የጡንቻዎች መወራጨት ብቻ ነው። ነገር ግን ከማህፀን ሲወጣ፡ እግዚአብሔር የሕይወትን እስትንፋስ እፍ ይልበታል፡ ከዚያም ይጮኻል። አያችሁ፡ ተ—ተፈጥሯዊ አካል እየተሰራ እንዳለ እርግጠኛ እንደሆንነው ሁሉ፡ ልክ ወደዚህ ሲመጣ እርሱን የሚቀበል መንፈሳዊ አካል አለ።

78 ከዚያም፡ አንድ ሰው፡ ከሰማይ ዳግመኛ ሲወለድ፡ በክርስቶስ ውስጥ የመንፈስ ህፃን ይሆናል።

ከዚያም፡ ይህ የሥጋ፡ መጎናጸፊያ ሲጣል፡ የምንሄድበት ተፈጥሯዊ አካል፡ ቲዮፋኒ፡ በእጅ ያልተሰራ፡ እኛ ሄደን የምንገባበት፡ ከሴትም ያልተወለደ አካል ነው።

ከዚያም ያ አካል ተመልሶ መጥቶ የከበረውን አካል ያነሳል።

ኢየሱስ ሲሞት ወደ ሲኦል የሄደውና፡ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት የሰበከውም ለዚህ ነው፥ ወደዚያው ቲዮፋኒ ተመልሶ ነበረና። ኦህ፡ ድንቅ ነው! እግዚአብሔር ይመስገን!

79 2ኛ ቆሮንቶስ 5፥1፡ “ይህ ምድራዊ አካል፡ ይህ ምድራዊ ድንኳን ቢፈርስ፡ ሌላ አለን” ይላል። አያችሁ፡ አዳም እንዳደረገው፡ በኃጢአት እንፈተንና እንፈተሽ ዘንድ፡ ሥጋ ለመሆን ስንል፥ ቀጥታ ከእግዚአብሔር፡ ከባህርይው በመምጣት፡ ያንን ዘልለን አልፈናል። ነገር ግን የቃሉ ፈተና ሲያበቃ፡ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ለእኛ ወደተዘጋጀልን ወደዚህ አካል እንወሰዳለን። እኛ ልንፈተንና ልንፈተሽ፡ በቀጥታ ወደዚህች ምድር ለመውረድ ስንል፡ የተሻገርነው በዚያ ያለውን ቃል ነው። በዚያ ውስጥ መጥተን ቢሆን ኖሮ፡ ምንም ፈተና ባልኖረ ነበር፥ ሁሉንም ነገር እናውቅ ነበር። ኢየሱስ ሥጋ ከመሆኑ በፊት ቃል ስለነበረ፡ ሁሉን ነገር ያወቀበት ምክንያት ይህ ነው። ከዚያም እኛ ቃል እንሆናለን።

80 እዚህ ከመጀመሪያው ጀምሮ የቃሉ ተካፋይ እንድንሆንና፡ ቃሉን እንድንመገብ፡ አስቀድመን በመወሰናችን፡ በቃሉ መልክ ተሰራን። ጉዟችሁን በጀመራችሁበት ጊዜ፡ ከመጀመሪያው አንስቶ በውስጣችሁ የነበረችውን ያቺን

ትንሽ የሕይወት ብልጭታ አያችሁ? ብዙዎቻችሁ ሊታስታውሱ ትችላላችሁ። **ይህን** ቤተክርስቲያን ተቀላቀላችሁ **ያንንም** ቤተክርስቲያን ተቀላቀላችሁ፡ **ይህንና ያንን** ሞከራችሁ፥ ምንም ሊያረካችሁ አልቻለም። በትክክል። ነገር ግን አንድ ቀን አስተዋላችሁት። በትክክል።

81 በቀደም ምሽት አንድ ቦታ እያስተማርኩ ነበር፡ ካሊፎርኒያ ወይም አሪዞና ውስጥ ይመስለኛል፡ ስለ... እዚህ ይህችን አጭር ታሪክ የነገርኳችሁ ይመስለኛል፡ እንዲት ዶሮ እንቁላል እንድታቅፍ ስላደረገውና ከስሯም የንስር እንቁላል ስላስቀመጠው ሰው። ያም ንስር ሲፈለፈል፡ እነዚያ ጫጩቶች አይተውት የማያውቁት እጅግ-አስቂኝ መልክ ያለው ወፍ ነበረ። ነገር ግን፡ ወዲያና ወዲህ ይራመድ ነበር። በ—በመካከላቸው እጅግ አስቀያሚው እርሱ ነበረ፡ ምክንያቱም ያቺ ዶሮ እንዴት እያቋቋች በዚያ የፍግ ክምር ላይ እየጫጨረች እንደምትበላ ሊረዳ አልቻለም ነበር። ሀሳቡ ሊገባው አልቻለም። እሷም፡ "የኔ ማር፡ ወደዚህ ናና ብላ" ትለው ነበር! ዳሩ ግን እ—እርሱ ንስር ነበረ፥ እርሱ እንደዚያ አይበላም። ያ የእርሱ ምግብ አልነበረም።

82 ስለዚህ አንበጣዎችንና-ሌሎችንም ነገሮች ትይዝና፡ ታውቃላችሁ፡ ትናንሽ ጫጩቶችን ትጠራለች። እነዚያ ትናንሽ ጫጩቶችም ሁሉ አብረው ይሄዳሉ፡ እያቋቋም፡ ይበላሉ። ያ ትንሽ ንስር ግን ያንን ማድረግ አልቻለም። ለእርሱ ል—ልክ አልመሰል አለው።

ስለዚህ አንድ ቀን እናቱ ልትፈልገው መጣች።

83 የዚያችን ዶሮ ማቋቋት ይሰማል። እንደ እሷ ለማቋቋት የቻለውን ሁሉ ይሞክራል፡ ነገር ግን አልቻለም። እንደ ጫጩት ለመጮህ ሞከረ፡ ነገር ግን አልቻለም። አያችሁ፡ እርሱ ንስር ነበረ። እርሱ፡ ከመጀመሪያውኑ፡ ንስር ነበረ። ከዶሮ ስር ብቻ ነው የተፈለፈለው።

ይህ ልክ እንደ አንዳንድ የቤተክርስቲያን አባላት ነው። እያንዳንዱ... ነገሩ ልክ እንደዚህ ነው፥ ታቅፎ ከተፈለፈለው ውስጥ፡ ትክክል የሚሆነው አንዱ ብቻ ነው።

84 ነገር ግን አንድ ቀን እናቱ በላዩ ላይ በረረችና፡ ጮኸች። እርሱም ድምፁን ለየው። ያ ትክክለኛ ድምፅ ሆኖ ተሰማው። ለምን? ከመጀመሪያውኑ፡ እርሱ ንስር ነበረና።

ወንጌልም፡ ወይም ቃሉም፡ ወይም የኢየሱስ ክርስቶስ ኃይልም ልክ እንደዚሁ ነው። አንድ ሰው ለዘላለም ሕይወት አስቀድሞ ከተወሰነ፡ ያንን የእግዚአብሔርን እውነተኛ ድምፅ፡ ጩኸት ሲሰማ፡ ምንም ነገር ከእርሱ ሊከለክለው አይችልም።

ቤተክርስቲያን፡ "የተአምራት ዘመን አልፏል" ትል ይሆናል፡ ቋ፡ ቋ፡ ቋ። "እዚህ ቁምና **ይህን** ብላ፡ እዚያ ቁምና **ያንን** ብላ።"

85 ያ የዶሮ ግቢ ውስጥ ያለ ነገር፡ ከእንግዲህ ወዲህ ለእርሱ አይሆንለትም። ጥሎ ሄዷል! "ሁሉም ነገር ይቻላል!" ከመሬት ተነሳ።

ዛሬ በብዙ ክርስቲያኖች ላይ ያለው፡ ችግር ይኸው ነው፡ እግሮቻቸውን ከመሬት ማንሳት አይችሉም።

እናቲቱም፡ “ልጄ፡ ዝለል! አንተ ንስር ነህ። እኔ ወዳለሁበት ወደዚህ ወደ ላይ ና” አለችው።

እርሱም፡ “እማዬ፡ በሕይወቴ፡ ዘልዬ አላውቅም” አላት።

86 እሷም፡ “መልካም፡ ዝለል እንጂ! ከመጀመሪያውኑ፡ አንተ ንስር ነህ። ጫጩት አይደለህም” አለችው። ስለዚህ ለመጀመሪያ ጊዜ ዘለለና ክንፎቹን አርገበገበ፥ ያን ያህል የተዋጣለት ባይሆንም፡ ነገር ግን ከመሬት ተነሳ።

እኛም የምናደርገው እንደዚሁ ነው። እግዚአብሔርን በእምነት፡ በተጻፈው ቃል እንቀበላለን። በዚያ ውስጥ የሆነ ነገር አለ፥ ያም የዘላለም ሕይወት ነው። ለዚህም አስቀድማችሁ ተወስናችኋል።

87 አያቱና ቅድመ አያቶቹ ንስሮች ነበሩ። ወደ ኋላ ትውልዱን ብንቆጥር፡ ሙሉ በሙሉ ንስር ነበረ። ንስር ከሌሎች ነገሮች ጋር አይቀላቀልም። እርሱ በፍጹም ዲቃላ አይደለም፡ እርሱ ንስር ነው።

88 ከዚያም፡ የእግዚአብሔር ቃል ራሱ የንስር ምግብ መሆኑን ካወቃችሁ በኋላ፡ ያንን ሌላውን ነገር ትታችሁ ወጣችሁ። ከዚያም የሕያው እግዚአብሔር ሕያው መልክ ሆናችሁ ተሰራችሁ። ከቲዮፋኒያችሁ ሰማችሁ። “ይህ ምድራዊ አካል ቢፈርስ፡ የሚጠብቀን ሌላ አለን።”

እናንተም፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ይህ ልክ ነውን” ትሉ ይሆናል?

መልካም፡ ጥቂት ንስሮችን እንውሰድና ለጥቂት ደቂቃዎች እንመልከታቸው። ሙሴ የሚባል፡ አንድ ሰው ነበረ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ነቢይ ንስር ተብሎ እንደሚጠራ ሁሉም ያውቃል።

89 ሙሴ የሚባል አንድ ነቢይ ነበረ። አንድ ቀንም እግዚአብሔር ጠራው፡ ወደ ምድሪቱም እንዲሻገር አልፈቀደለትም፡ እ—እርሱም በዓለት ላይ ሞተ። መላእክትም ወስደው ቀበሩት።

መሞት እንኳን ያላስፈለገው ሌላ ሰው፡ ሌላ ንስር ነበረ። እርሱ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ሄደ፡ እግዚአብሔርም ሰረገላን ወደ ታች ላከ፥ ይህንንም የሥጋ መጎናጸፊያ ጥሎ፡ ወደ ላይ ወጥቶ የዘላለምን ሽልማት ተቀዳጀ።

ከስምንት መቶ ዓመታት በኋላ፡ ከስምንት መቶ ዓመታት በኋላ፡ ክብሩ በተገለጠበት ተራራ ላይ፡ እነዚያ ሁለት ሰዎች እዚህ ቆመው ነበረ። የሙሴ ሥጋ ለመቶዎች ዓመታት በሰብሶ ነበረ፡ ዳሩ ግን እዚህ ጴጥሮስ፡ ያዕቆብና፡ ዮሐንስ እንኳን ሊያውቁት በሚችሉበት መልክ ነበረ። አሜን! “ይህ ምድራዊ ድንኳን ቢፈርስ፡” በዚህች ምድር ላይ የተገለጻችሁ የእግዚአብሔር ባህርይ ከሆናችሁ፡ “ከዚህ ዓለም ስትለዩ የሚጠብቃችሁ ሌላ አካል አላችሁ።” እነርሱ በቲዮፋኒ አካላቸው፡ በመገለጥ ተራራ ላይ፡ ቆመው ነበረ። ምክንያቱም፡ ቃሉ የመጣላቸው ነቢያት ነበሩና።

90 እንዲሁም በአንድ ወቅት የነበረን፡ ሳሙኤል የተባለ፡ ሌላ ነቢይ እንመልከት። እርሱ ታላቅ ሰው ነበረ። እስራኤልን አስተምሮ ነበረ፥ ንጉሥ ሊኖራቸው እንደማይገባም ነግሯቸው ነበረ። እርሱም፡ “በጌታ ስም አንድ ነገር ነግሬአችሁ ሳይፈጸም የቀረበት ጊዜ አለን” አለ?

እነርሱም፡ “የለም። በጌታ ስም ሁልጊዜ የተናገርከው ሁሉ ተፈጽሟል” አሉት።

እርሱ ነቢይ ነበረ፡ ሞተም።

91 ከሦስት ወይም አራት ዓመታት ገደማ በኋላ፡ ንጉሡ ችግር ውስጥ ወደቀ፥ ያም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከመፍሰሱ በፊት ነበረ። እርሱ በገነት ውስጥ ነበረ። የዓይንዶርዋ ጠንቋይም፡ መጥቶ ሳኦልን የሚያጽናና ሰው ጠራች። ጠንቋይቱም እርሱን ቆሞ ባየችው ጊዜ፡ “አማልክት ከምድር ሲወጣ አያለሁ፡” አለች።

92 ያም ሰው ከሞተ፡ ከተቀበረና፡ በመቃብር ውስጥ ከበሰበሰ በኋላ፡ የነቢይነት መጎናጸፊያውን ለብሶ፡ በዚያ ዋሻ ውስጥ ቆሞ ነበረ፡ አሁንም ነቢይ ነበረ። አሜን። ምክንያቱም፡ “የእግዚአብሔር ጠላት እንደሆንክ እያወቅህ፡ ለምን ከዕረፍቴ ጠራኸኝ” አለው? ትንቢት ሲናገር ተመልከቱ። “ነገ ማታ፡ በዚህ ሰዓት፡ ከእኔ ጋር ትሆናለህ።” ከዚህ ሥጋው ቢለይም፡ አሁንም ነቢይ ነበረ።

አያችሁ፡ እርሱ በዚህ ሰፍራ የዚያ ቃል አካል ሆኖ ነበረ፡ ከሥጋ ሕይወትም ወጥቶ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ለእርሱ ወደተዘጋጀለት አካል ተመልሶ ገባ። ወደ ቲዮፋኒ ገባ፡ ያም ቃሉ ነበረ። ገባችሁን? አማኞች ሁሉ ከዚህ ሰናልፍ የምንሄደው ወደዚያ ነው።

93 ከዚያም፡ በዚያ መልክ ሲሆን፡ መጋረጃው ይነሳል። አያችሁ፡ ወደዚያ ስትገቡ፡ እናንተም ደግሞ፡ ቃል ናችሁ። ልክ እንደ ትንሹ ህፃን፥ ከጥቂት ጊዜ በፊት እንደተናገርኩት...

94 አሁን አስተውሉ። እነዚህን ነገሮች ለማወቅ፡ ስለተከፈቱት ማኅተሞች እግዚአብሔር ይመስገን፡ ጸሎቴም ይኸው ነው!

95 አሁን እውነተኛው የመልከ ጼዴቅ መገለጥ ወደ እይታ ይመጣል። ምንድን ነው? እርሱ ሥጋ ከመሆኑ በፊት፡ እግዚአብሔር፡ ቃል ነበረ፥ እግዚአብሔር፡ ቃሉ። ምክንያቱም፡ እርሱ መሆን ነበረበት፥ እንደ እርሱ የማይሞት ሊሆን የሚችል ሌላ ማንም አልነበረምና። አያችሁ፡ እኔ አባትና እናት ነበሩኝ፥ እናንተም፡ እንዲሁ ነበሯችሁ። ኢየሱስም አባትና እናት ነበሩት። “ይህ ሰው ግን አባት አልነበረውም፡ ወይም እናትም አልነበረችውም።” ኢየሱስ የተጀመረበት ጊዜ ነበረው፥ ይህ ሰው ግን አልነበረውም። ኢየሱስ ሕይወቱን አሳልፎ ሰጠ፥ ይህ ሰው ግን ሕይወት ራሱ ስለነበረ፡ ያንን ማድረግ አይችልም ነበረ። ሁልጊዜም ያው ተመሳሳይ-ሰው ነው። እግዚአብሔር እንደሚገልጥላችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። ሁልጊዜም፡ ያው-አንድ አካል ነው።

96 አሁን ማዕረጉን አስተውሉ፡ “የጽድቅ ንጉሥ።” አሁን፡ ዕብራውያን 7፥2፡ “የጽድቅ ንጉሥ፡ የሰላምም ንጉሥ።” እርሱ ሁለት ነገሥታት ነው። አሁን ተመልከቱ፡ ዕብራውያን 7፥2፡ “የጽድቅ ንጉሥ፡ እንዲሁም ደግሞ የሰላም ንጉሥ።” በዚያ ላይ እርሱ ሁለት ነገሥታት ነው። አሁን በሥጋ መጥቶ አካሉን ወደ ላይ ከተቀበለ በኋላ፡ በራእይ 21፥16 ላይ፡ “የነገሥታት ንጉሥ፡” ተብሎ ተጠርቷል። እርሱ፡ ሦስቱም በአንድ ላይ ነው። አያችሁ፡ ንጉሥ እግዚአብሔር፥ ንጉሥ ቲዮፋኒ፥ ንጉሥ ኢየሱስ። “እርሱ የነገሥታት ንጉሥ ነው።”

ልክ ነፍስ፡ ሥጋና መንፈስ አንድ ለመሆን፡ በአንድነት እንደሚገናኙት ሁሉ፡ እነዚህም ሁሉም በአንድነት ተገናኝተዋል።

97 እንዲሁም ደግሞ፡ እርሱ አብ ነው፡ ያም የመጀመሪያው ነበረ፥ ወልድ፥ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ፡ መንፈሱ።

“የጽድቅ ንጉሥ፡” የመንፈስ ባህርይ፥ ቲዮፋኒ፡ “የ—የሰላም ንጉሥ፡” ቲዮፋኒ፥ በሥጋም ጊዜ እርሱ “የነገሥታት ንጉሥ” ነበረ፡ ያው አንድ አካል ነው።

98 በቲዮፋኒ ጊዜ፡ ሙሴ ሲያየው፡ ዘጸአት 33፥2፣ እርሱ ቲዮፋኒ ነበረ። ሙሴ እግዚአብሔርን ለማየት ፈልጎ ነበረ። ድምፁን ሰምቶ ነበረ፡ ሲያነጋግረውም ሰምቶት ነበረ፡ በዚያ ቁጥቋጦ ውስጥ እንደ ታላቅ የእሳት ዓምድ ሆኖ፡ አይቶት ነበረ። እርሱም፡ “አንተ ማን ነህ? ማን እንደሆንክ ማወቅ እፈልጋለሁ” አለ። ሙሴ ነው ያለው። “ማየት... ” “እንዳይህ ከፈቀድክልኝ፡ ፊትህን ማየት እፈልጋለሁ።”

99 እርሱም፡ “ማንም ሰው ፊቴን ሊያይ አይችልም” አለው። አክሎም፡ “እጄን በዓይኖችህ ላይ አደርጋለሁ፡ እኔም አልፋለሁ። ጀርባዬንም ታያለህ፡ ፊቴን ግን አታይም” አለው። አያችሁ? ይህንንም ባደረገ ጊዜ፡ የሰው ጀርባ ነበረ፥ እርሱ ቲዮፋኒ ነበረ። ከዚያም ወደ ሙሴ የመጣው ቃል፡ “**እኔ ነኝ**፡” ያ ቃል ነበረ። ቃሉ ወደ ሙሴ በሚነድ ቁጥቋጦ ውስጥ በእሳት ዓምድ መልክ መጣ፡ እርሱም “**እኔ ነኝ**” ነበረ።

100 ልክ እንደ ሥነ መለኮት ቃል፡ ማለቴ፡ ከቲዮፋኒ፡ ይቅርታ አድርጉልኝ፡ ከአድባሩ ዛፍ ስር፡ እንደ ሰው ሆኖ ወደ አብርሃም መጣ። አሁን እዚያ ላይ ተመልከቱ። ወደ አብርሃም አንድ ሰው መጣ፡ ሦስት ነበሩ፡ ከአድባሩም ዛፍ ስር ተቀመጡ፡ ሦስት ነበሩ። አብርሃምንም ካነጋገረው በኋላ፡ አስተውሉ...

101 ለምን መጣ? አብርሃም፡ የተሰፋውና ስለሚመጣው ልጅ መልእክት ያለው ሰው ስለነበር፡ እንዲሁም ተቃራኒ የሆነውን ማንኛውንም ነገር እንዳልነበረ አድርጎ በመጥራት፡ በእግዚአብሔር ቃል የታመነ የእግዚአብሔር የቃል-ነቢይ ስለነበረ ነው። ቃሉ እንዴት ፍጹም እንደሆነ አያችሁ? ቃሉ ወደ ነቢዩ መጣ። አያችሁ፡ እዚያ እግዚአብሔር በቲዮፋኒ ውስጥ ነበረ። መጽሐፍ ቅዱስም፡ “ቃሉ ወደ ነቢዩ ይመጣል” ይላል። ይሄውና ቃ—ቃሉ በቲዮፋኒ ውስጥ።

አሁን እናንተ፡ “ያ እግዚአብሔር ነበረን” ትላላችሁ?

102 አብርሃም እርሱ እንደሆነ ተናግሯል። ሰሙ... ኤሎሂም ብሎ ጠራው። አሁን፡ በዘፍጥረት 1 ላይ፡ “በመጀመሪያ **ኤሎሂም** ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ” ብሎ እንዳለ፡ ታገኛላችሁ። በዘፍጥረት 18 ላይ ደግሞ፡ አ—አብርሃም በዚያ የተቀመጠውንና ያነጋገረውን፡ የልቡንም ምስጢር ሊነግረው የቻለውን፡ ከኋላው ሳራ ምን እያሰበች እንደነበረ የነገረውን ይህንን አካል፡ “ኤሎሂም” ብሎ እንደጠራው፡ እናውቃለን። እርሱ በቲዮፋኒ መልክ ነበረ። ገባችሁን? አስተውሉ...

103 አሁን እርሱ በዚያን ጊዜ በቲዮፋኒ መልክ እንደነበረ እናውቃለን። እርሱንም፡ “ጌታ እግዚአብሔር፡ ኤሎሂም” ብሎ ጠራው። አሁን፡ በዘፍጥረት 18 ላይ፡ ያ እውነት እንደሆነ እናገኛለን።

104 አሁን አስተውሉ፡ አብርሃም... ሦስቱ በአንድ ላይ ነበሩ፡ ዳሩ ግን አብርሃም ሦስቱን ባገኛቸው ጊዜ፡ “ጌታዬ፡” አለ።

ነገር ግን ሎጥ፡ በሰዶም ሳለ፥ ሁለቱ ወደዚያ ወረዱ፡ ሎጥም ሁለቱ ሲመጡ ባየ ጊዜ፡ “ጌቶቼ፡” አለ። አያችሁ፥ ችግሩ ምን ነበረ? በመጀመሪያ ደረጃ፡ ሎጥ ነቢይ አልነበረም፡ በትክክል፡ ወይም የዘመኑ መልእክተኛ

አልነበረም፡ ስለዚህ ስለ እርሱ ምንም ዓይነት መገለጥ አልነበረውም። ይህ ፍጹም ትክክል ነው። ሎጥ "ጌቶች" ብሎ ሊጠራቸው ይችላል። ብዙ ቢሆኑም እንኳን፡ አሁንም "ጌቶች፡" ይል ነበር።

ነገር ግን አብርሃም ምንም ያህል ብዙ ቢያይም፡ አሁንም አንድ ጌታ ብቻ ነበረ። እግዚአብሔር እዚያ አለ። ይህም መልከ ጼዴቅ ነበረ።

105 አስተውሉ፡ ጦርነቱ ካበቃ በኋላ፡ መልከ ጼዴቅ ድል አድራጊ ለሆነው ልጁ የጌታ እራት አቀረበለት፥ ይህንን አሰቡት፡ የራሱ አካል የሆነውን! አሁን እዚህ ላይ ማየት እንፈልጋለን። እዚህ ላይ በምሳሌነት፡ የምናየው፡ የጌታ እራትን ነው። ከጦርነቱ በኋላ፡ ከራሱ አካፍሎ ሰጠው፡ ምክንያቱም የጌታ እራት የክርስቶስ አካል ነውና። ትግሉ ካበቃ በኋላ፡ ራሳችሁን አሟጣችሁ ከሰጣችሁ በኋላ፡ ያኔ ነው ከክርስቶስ የምትካፈሉት፡ የዚህ አካል ክፍል የምትሆኑት። ተረዳችሁ?

106 ያዕቆብ ሌሊቱን ሙሉ ታገለ፡ እስኪባርከውም ድረስ አልለቀቀውም። በትክክል። ለሕይወት ተዋጋ! ውጊያው ካበቃ በኋላም፡ እግዚአብሔር ከራሱ ያካፍላችኋል። እውነተኛው የጌታ እራት ይህ ነው። ትንሹ ዳቦና ቂጣ ይህንን የሚወክል ብቻ ነው። ታግላችሁ የእግዚአብሔር አካል እስካልሆናችሁ ድረስ ይህንን ልትወስዱት አይገባም።

107 አስታውሱ፡ በዚህን ጊዜ፡ የጌታ እራት ገና አልተመሰረተም ነበር፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ በርካታ ዓመታት አልፈው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት እስኪደርስ ድረስ አልተጀመረም ነበር።

108 ነገር ግን ልጁ አብርሃም ድልን ከተቀዳጀ በኋላ፡ መልከ ጼዴቅ ተገናኝቶት የወይን ጠጅና ዳቦን ሰጠው፥ ይህም የሚያሳየው ይህ ምድራዊ ውጊያ ካበቃ በኋላ፡ በሰማያት እርሱን አግኝተነው ዳግመኛ የጌታ እራት እንደምንወስድ ነው። ያም የሰርግ እራት ይሆናል። "በአባቴ መንግሥት፡ ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ፡ አዲሱን እስከምጠጣበት፡ እስከዚያ ቀን ድረስ፡ ከዛሬ ጀምሬ አልጠጣውም።" ልክ ነው?

109 እንደገና አስተውሉ፡ አብርሃም ወደ ቤቱ ከመመለሱ በፊት መልከ ጼዴቅ ሊያገኘው ሄደ። እዚህ እንዴት ያለ ድንቅ ምሳሌ አለን! ከጦርነቱ በኋላ አብርሃም ወደ ቤቱ ከመመለሱ በፊት፡ መልከ ጼዴቅ አገኘው።

እኛም ወደ ቤታችን ከመድረሳችን በፊት፡ ኢየሱስን በአየር ላይ እናገኘዋለን። በትክክል። ሁለተኛ ተሰሎንቄ ይህንን ይነግረናል፡ ምክንያቱም፡ "በአየር ላይ ከእርሱ ጋር እንገናኛለንና።" ርብቃ በመሸ ጊዜ ይስሐቅን፡ በሜዳ ላይ፡ እንዳገኘችው ያለ ድንቅ ምሳሌ ነው። "በአየር ላይ ከእርሱ ጋር እንገናኛለን።" ሁለተኛ ተሰሎንቄ እንዲሁ ይነግረናል። "ሕያዋን ሆነን የምንቀረውም ያንቀላፉትን አንቀድምም፥ የእግዚአብሔር መለከት ይነፋልና፡ በክርስቶስ የሞቱትም አስቀድመው ይነሳሉ፥ ሕያዋን ሆነን የምንቀረውም፡ ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በአንድነት እንነጠቃለንና።" እነዚህ ምሳሌዎች ሁሉ፡ ፍጹም ናቸው።

110 ስለዚህ፡ ቲዮፋኒው፡ ሞታችሁ ወደዚያ ቲዮፋኒ ውስጥ ከገባችሁ፡ (ምን ይከሰታል?) ያንን የተዋጀውን አካል ለማንሳት ቲዮፋኒው ወደ ምድር ይመጣል። እዚህ አየር ላይ ከሆናችሁም፡ ቲዮፋኒውን ለመገናኘት አካሉን

ይዛችሁ ትሄዳላችሁ፡ ይሄውና፡ “ተነጥቃችሁም፡ ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል ትሄዳላችሁ።”

111 ይህ መልከ ጼዴቅ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ማን ነው!

112 አሁን እዚህ የሕይወታችንን ጉዞ፡ የሞታችንንና፡ ከሞትን በኋላ ወዴት እንደምንሄድ የሚገልጸውን ሙሉ ምስጢር በግልጽ እናያለን። እንዲሁም፡ አስቀድሞ መወሰን እዚህ ላይ በግልጽ ይታያል። አሁን ይህንን ስናስተምር፡ በደንብ አዳምጡ።

113 በምስጢር ይዞት የነበረው የ—የእርሱ የዘላለም ዓላማ ደረጃዎች አሁን ተገልጠዋል። አስተውሉ፡ ወደ ፍጽምና የሚያደርሱ ሦስት ደረጃዎች አሉ። ዓለምን እንደተበዝበት ሁሉ፡ ቤተክርስቲያኑንም በዚያው መንገድ ይዋጃታል፡ ሰዎችንም፡ በሦስት ደረጃዎች ይዋጃል። አሁን ተመልከቱ። አንደኛው ልክ ሉተር እንደሰበከው፡ መጽደቅ ነው፥ ሁለተኛው፡ ዌስሊ እንደሰበከው፡ መቀደስ ነው፥ ሦስተኛው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። ልክ ነው። ከዚያም ንጥቀት ይመጣል!

114 አሁን፡ ዓለምን፡ ዓለምን እንዴት ተበዠ? መጀመሪያ፡ ያደረገው ነገር፡ ኃጢአት በሰራች ጊዜ፡ በውሃ ጥምቀት አጥቦ አጸዳት። በትክክል። ከዚያም ከመስቀል ላይ ደሙን አፈሰሰላት፡ ቀደሳትም፡ የራሱም ብሎ ጠራት። ከዚያስ በኋላ ምን ያደርጋል? ዓለምን ሁሉ ከእናንተ ውስጥ ነቅሎ አውጥቶ፡ በእሳታማው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መላውን ማንነታችሁን እንዳደሰው ሁሉ፡ ዓለምንም እንዲሁ ያድሳታል። በእሳትም ትቃጠላለች፡ በሚሊዮን ማይሎች ከፍታ ላይ ያለውን፡ እያንዳንዱን ጀርም ያጸዳዋል፡ ሁሉም ነገር ጸድቶ ይወገዳል። ከዚያም አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይሆናል፡ ልክ መንፈስ ቅዱስ ሲይዛችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት እንደምትሆኑት ማለት ነው። አያችሁ፡ ይኸውና፡ ነገሩ ሁሉ እጅግ ግልጽ ነው። ሁሉም ነገር በሦስት ነው።

115 ተፈጥሯዊው ልደት በሦስት ነው። ልጅ ለምትወልድ ሴት መጀመሪያ የሚፈጠረው ነገር ምንድን ነው? መጀመሪያ ምን ይፈሳል? ውሃ። ቀጥሎስ ምን ይፈሳል? ደም። ቀጣዩስ ሂደት ምንድን ነው? ሕይወት። ውሃ፡ ደም፡ መንፈስ።

በእጽዋትስ ላይ ምን ይከሰታል? ይበሰብሳሉ። የመጀመሪያው ነገር ምንድን ነው? አገዳ። ቀጣዩስ? ዝራረት። ቀጣዩስ? ቅርፊቱ። ከዚያም እህሉ፡ አያችሁ፡ ከዚያ ውስጥ ይወጣል። ወደ እህሉ እስኪደርስ ድረስ፡ ልክ ሦስት ደረጃዎች አሉት። ፍጹም ልክ ነው።

116 እግዚአብሔር ያንን ያጸናዋል። ያ ሁልጊዜም ትክክል ነው። እግዚአብሔር እውነት መሆኑን ያጸናዋል። በግልጽ እንደሚያሳየው፡ በቤዛነት ውስጥ የሚታሰበው አስቀድሞ የተወሰነው ብቻ ነው። ተረድታችኋልን? ያንን ደግሜ ልናገረው። በቤዛነት ውስጥ የሚታሰበው አስቀድሞ የተወሰነው ብቻ ነው። ሰዎች የዳኑ አስመሰለው፡ እንደዳኑ ያሰቡ ይሆናል፡ ሆኖም እውነተኛው ቤዛነት አስቀድመው ለተወሰኑት ነው። ምክንያቱም፡ **ቤዛነት** የሚለው ቃል ራሱ ትርጉሙ “ወደ ነበረበት መመለስ” ማለት ነውና። ልክ ነው? **መዋጀት** ማለት... ማንኛውንም ነገር **መዋጀት፡** ማለት፡ “ወደ መጀመሪያ ስፍራው መመለስ።” ሃሌሉያ! ስለዚህ የሚመለሰው አስቀድሞ የተወሰነው ብቻ ነው፡ ምክንያቱም ሌሎቹ ከዚያ አልመጡምና። አያችሁ፡ “ወደ ነበረበት መመለስ!”

117 ከመጀመሪያው አንስቶ፡ ከእርሱ ጋር ዘላለማዊ በመሆን... ያላችሁ የዘላለም ሕይወት፡ የእርሱ ሀሳብ ስለነበራችሁ ነው፡ እርሱ እንድትሆኑ የፈለገው፡ ብቸኛው... እኔ እዚህ መድረክ ላይ እንድቆም ፈለገ፡ እንበል። እናንተም ዛሬ ማታ እዚያ ወንበር ላይ እንድትቀመጡ ፈለገ። ስለዚህ እያገለገልን ያለነው የእርሱን የዘላለም ዓላማ ነው። ያም ቤቱን ትቶ የወጣው፡ ወደ ምድር የመጣው የእርሱን ዓላማ ለማገልገል ብቻ ነው። ልክ ነው? መልካም። ከዚያም፡ ስራው ሲጠናቀቅ፡ ወደ ከበረ ሁኔታ ይመለሳል፥ በስሎ ዳግመኛ ይመለሳል።

118 አንገቱን ሊቆርጡ ግንዱን ሲያዘጋጁ፡ ጳውሎስ እንዲህ ማለቱ አያስገርምም፥ እንዲህ አለ፡ “ሞት ሆይ፡ መውጊያህ የት አለ? መቃብር ሆይ፡ ድል መንሳትህ የት አለ? ነገር ግን ድልን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን!” እርሱም፡ “ሞት ሆይ፡ እንድጮህ ማድረግ የምትችለው የት እንደሆነ ንገረኝ! መቃብር ሆይ፡ እንዴት እንደምትይዘኝ ንገረኝ! እኔ የዘላለም ሕይወት፡ ባለቤት ነኝና” አላቸው። አሜን! ይህንን አውቆት ነበረ። ሞት፡ ሲኦል፡ መቃብር፡ ምንም ሊይዘው አልቻለም። የዘላለም ሕይወት እስካለን ድረስ፡ ምንም ሊጎዳን አይችልም! በዘላለም ሕይወት እንደተባረከ ተረድቶ ነበረ።

119 ልክ እንደ አንዲት ትንሽ የጤዛ ጠብታ ነው። እንደገባኝ ከሆነ፡ እ... እኔ ስለ ኬሚስትሪ ያን ያህል አላውቅም። ነገር ግን፡ የ—የእርጥበት ወይም የአየር ንብረት መርጋት መሆን አለበት። ሌሊቱ ሲመሽና ሲጨልም፡ ከሰማይ ይወርድና መሬት ላይ ይንጠባጠባል። ከሆነ ቦታ ይወድቃል። ነገር ግን በማግስቱ ጠዋት ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት፡ ያች ትንሽ ጠብታ፡ እዚያ ላይ ወድቃ፡ ትንቀጠቀጣለች። ነገር ግን ፀሐይ እስክትወጣ ተውአት፡ እንዴት እንደምታንጸባርቅ ተመልከቱ። ደስተኛ ትሆናለች። ለምን? ፀሐይዋ ወደመጣችበት ስፍራ ቀጥታ መልሳ ልትጠራት ስለሆነ ነው።

ክርስቲያንም ልክ እንደዚሁ ነው። ሃሌሉያ! ወደ እግዚአብሔር ህልውና ስንገባ፡ ከሆነ ቦታ እንደመጣንና፡ ወደዚያም በሚስበን ኃይል ዳግመኛ ተመልሰን እንደምንሄድ በውስጣችን የሆነ ነገር ይነግረናል ይህንንም እናውቃለን።

120 ያች ትንሽ የጤዛ ጠብታ፡ ታንጸባርቃለች ታበራለች ትጮኻለችም፡ ምክንያቱም ከላይ እንደመጣች ታውቃለች፡ ያቺም ፀሐይ ዳግመኛ ወደ ላይ አውጥታ እንደምትወስዳት ታውቃለችና።

የእግዚአብሔር ባህርይ የሆነ፡ ከእግዚአብሔር የተወለደም ሰው፡ ሁሉ፡ ሃሌሉያ፡ ከእግዚአብሔር ልጅ ጋር ሲገናኝ፡ አንድ ቀን ከዚህ ወደ ላይ እንደሚወስድ ያውቃል። “እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ፡ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ።” አሜን!

121 አሁን፡ አስተውሉ፡ አሁን መልከ ጼዴቅን እናያለን ማርያምም ለምን እናቱ እንዳልሆነች እንረዳለን። **እናቴ** ሳይሆን “አንቺ ሴት፡” ብሎ የጠራትም ለዚህ ነው። “አባት አልነበረውም፡” ምክንያቱም እርሱ አባት ነበረና፡ የዘላለም አባት፡ ሦስቱ በአንዱ ውስጥ ያለው ነው። “እናት አልነበረችውም፡” በእርግጥም አልነበረችውም። አባት አልነበረውም፡ እርሱ አባት ነበረና። አንድ ገጣሚ በአንድ ወቅት፡ ለኢየሱስ ታላቅ የሙገሳ ቃል ሲናገር፡ እንዲህ እንዳለው ነው፥

በሚነደው የእሳት ቁጥቋጦ ውስጥ ለሙሴ የተናገርኩት
እኔ ነኝ፡
የአብርሃም አምላክ፡ የሚያበራው የንጋት ኮከብ እኔ ነኝ።
አልፋና፡ ኦሜጋ፡ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።
ፍጥረቱ ሁሉ እኔ ነኝ፡ ስሙም ኢየሱስ ነው። (በትክክል።)

ኦህ፡ እኔ ማን እንደሆንኩ ትላላችሁ፡ ከወዴትስ
እንደመጣሁ ይላሉ፡
አባቴን ታውቃላችሁን፡ ወይስ ስሙን ልትነግሩ
ትችላላችሁ? (ሃሌሉያ!)

122 የአብ ስም ያ ነው! አዎ፡ "እኔ በአባቴ ስም መጥቻለሁ፡ አትቀበሉኝምም።" አያችሁ? በእርግጥም፡ እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው።

123 ይህም መልከ ጼዴቅ ሥጋ ሆነ። በመጣ ጊዜ እንደ ነቢይ፡ ራሱን የሰው ልጅ አድርጎ ገለጠ። እርሱ በሦስት የልጅ ስሞች መጣ፥ የሰው ልጅ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ የዳዊት ልጅ።

124 እዚህ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፡ መጽሐፍ ቅዱስን ለመፈጸም፡ ሰው ነበረ። ሙሴ፡ "ጌታ አምላካችሁ ከእናንተ መካከል እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሳላችኋል" ብሎ ነበረ። ስለዚህ እንደ ነቢይ መምጣት ነበረበት። እርሱ፡ "እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ" ብሎ በፍጹም በጭራሽ፡ ተናግሮ አያውቅም። "እኔ የሰው ልጅ ነኝ። በሰው ልጅ ታምናላችሁን፡" አለ እንጂ? ምክንያቱም፡ መመስከር የነበረበት ያንን ነበር፡ ያ ደግሞ ማንነቱ ነበር።

አሁን ደግሞ በሌላ የልጅ ስም መጥቷል፥ የእግዚአብሔር ልጅ፡ የማይታየው፡ መንፈስ።

ዳግመኛም ሲመጣ፡ በዙፋኑ ላይ ሊቀመጥ፡ የዳዊት ልጅ ይሆናል።

125 አሁን እዚህ በነበረበትና ሥጋ በሆነበት ጊዜ፡ "የሰው ልጅ፡" ተብሎ ተጠርቶ ነበረ። አሁን፡ የሰው ልጅና፡ ነቢይ እንደመሆኑ መጠን ራሱን ለዓለም እንዴት አሳወቀ?

126 አንድ ቀን ስለ ጴጥሮስና፡ ስለ ወንድሙ ስለ እንድርያስ ታሪክ እየተናገርኩ ነበር። እነርሱ ዓሣ አጥማጆች ነበሩ፡ አባታቸው ዮናስም ታላቅ የቀድሞ አማኝ ነበር። አንድ ቀን በጀልባዋ ዳር ተቀምጦ እንዲህ አላቸው አሉ። "ልጆቼ፡ ዓሣ ባስፈለገን ጊዜ እንዴት እንጸልይ እንደነበር ታውቃላችሁ፡" አላቸው። እነርሱ ዓሣ አጥማጅ ነጋዴዎች ነበሩ። እንዲህ አለ፡ "ለኑሯችን በእግዚአብሔር፡ በይሖዋ፡ ታምነናል። አሁን እያረጀሁ ነው፥ ከእናንተ ከልጆቼ ጋር ብዙ ጊዜ ልቆይ አልችልም። እኔም እንደ እውነተኛ አማኞች ሁሉ፡ ያ መሲሕ የሚመጣበትን ጊዜ፡ ሁልጊዜ ስጠባበቅ ኖሬአለሁ። ሁሉንም ዓይነት ሐሰተኛ መሲሆች አይተናል፡ አንድ ቀን ግን፡ እውነተኛው ይመጣል።" እንዲህም አለ፡ "ይህ መሲሕ ሲመጣ፡ እናንተ ልጆቼ እንድትታለሉ አልፈልግም። ይህ መሲሕ ዝም ብሎ የሥነ መለኮት ምሁር አይሆንም። እርሱ ነቢይ ይሆናል፡ ምክንያቱም እኛ የምንከተለው፡ ነቢያችን ሙሴ፡ ተናግሯልና" አላቸው።

አሁን፡ ማንኛውም አይሁዳዊ በነቢዩ ያምናል። ይህንን እንዲያውቅ ተምሯል። ነቢዩ የተናገረው ነገር ከተፈጸመ፡ ያ እውነት ነው። ነገር ግን

እግዚአብሔር፡ “በመካከላችሁ፡ መንፈሳዊ ወይም ነቢይ ቢኖር፡ እኔ ጌታ ራሴን እገልጥለታለሁ። የተናገረውም ቢፈጸም፡ ሰሙት ፍሩትም፥ ነገር ግን ካልተፈጸመ፡ በፍጹም አትፍሩት” አለ። አያችሁ? ስለዚህ ያ የ—የነቢዩ ማረጋገጫ ነበረ።

127 “ስለዚህ ሙሴ በእርግጥም የጸና ነቢይ ነበረ፡ እርሱም፡ ‘ጌታ አምላካችሁ ከወንድሞቻችሁ፡ መካከል፡ እንደ እኔ ያለ ነቢይ፡ ያስነሳላችኋል። እርሱንም የማይሰማ ሁሉ ከሕዝቡ ተለይቶ ይጠፋል’ አለ።” እርሱም፡ “አሁን፡ ልጆቼ፡ አስታውሱ፡ ይህም፡ እንደ ዕብራውያንነታችን፡ እኛ በእግዚአብሔር በጸኑ ነቢያት እናምናለን” አለ።

አሁን በጥሞና አዳምጡ። ይህ እንዲያመልጣችሁ። እንዲህም አለ፡ “መሲሑ ሲመጣ፡ ታውቁታላችሁ፡ ምክንያቱም እርሱ ነቢይ-መሲሕ ይሆናልና። አሁን፡ አራት መቶ ዓመታት እንዳለፉት ይናገራሉ። ከሚልክያስ ጀምሮ ነቢይ አልነበረንም፡ ነገር ግን እርሱ ይሆናል” አላቸው።

128 እርሱ ከሞተ፡ ከጥቂት ዓመታት በኋላ፡ አንድ ቀን፡ ልጁ እንድርያስ በወንዙ ዳርቻ ይንሸራሸር ነበር። በዚያም ከምድረ በዳ የመጣ አንድ ኃይለኛ ሰው፡ “ያ መሲሕ አሁን በመካከላችሁ ቆሟል፡” ሲል ሰማ! በምድረ በዳ የተነሳውና ወደዚያ የበረረው ያ ታላቅ ንስር፡ እንዲህ አለ፡ “መሲሑ አሁን በመካከላችሁ ነው። ገና አናውቀውም፡ ነገር ግን በመካከላችሁ ቆሟል። ከሰማይ የሚመጣ ምልክት ስለምመለከት፡ አውቀዋለሁ” አለ።

አንድ ቀንም እንዲህ አለ፡ “እነሆ፡ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ፡ የእግዚአብሔር በግ!”

ይህ ሰው... ወንድሙን ሊፈልግ፡ ሄደ። እርሱም፡ “ስምዖን፡ ወደዚህ እንድትመጣ እፈልጋለሁ፥ መሲሑን አግኝተነዋል” አለው።

“ኦህ፡ እንድርያስ፡ ተወኝ! አንተ ከዚህ የተሻለ ታውቃለህ!”

“ኦህ፡ አውቃለሁ። ነገር ግን፡ ያ፡ ይህ ሰው የተለየ ነው።”

“እርሱ የት ነው ያለው? ከየት ነው የመጣው? ”

“የናዝሬቱ ኢየሱስ።”

“ከዚያች ትንሽ፡ ክፉ ከተማ? እንዴ፡ እንደዚያ ካለ ክፉና ቆሻሻ ሰፍራ፡ ሊመጣ አይችልም።”

“መጥተህ እይ።”

129 በመጨረሻም አንድ ቀን እንዲመጣ አሳመነው። ስለዚህ በዚህ መሲሕ ፊት በመጣ ጊዜ፡ ኢየሱስ በዚያ ቆሞ፡ ለሕዝቡ ይናገር ነበር። ወደ ፊት ቀርቦ በቆመ ጊዜ፡ “ስምህ ስምዖን ነው፡ አንተም የዮናስ ልጅ ነህ፡” አለው። ያም ነገሩን ፈጸመው። የመንግሥቱን መክፈቻዎች አገኘ። ለምን? ያ ሰው እርሱን እንደማያውቀው አውቆ ነበርና። እርሱንና፡ እንዲሁም መሲሑን እንዴት ማመን እንዳለበት ያስተማረውን ያንን እግዚአብሔርን የሚፈራ አዛውንት አባት እንዴት ሊያውቅ ቻለ?

130 ፊልጶስ የሚባል አንድ ሰው፡ በዚያ ቆሞ ነበረ። ኦህ፡ እርሱ እጅግ ተደሰተ! መጽሐፍ ቅዱስን አብሮት ሲያጠና የነበረውን፡ ሌላ ሰው ያውቅ

ነበረ። ተነሰቶ፡ ኮረብታውን ዞሮ ሄደ፡ በወይራ ዛፎችም መሐል አገኘው። ተንበርክኮ፡ ይጸልይ ነበር። አብረው ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ተምረው ነበረ። ስለዚህ ወደዚያ መጣና እንዲህ አለው፡ ከጸሎቱ እንደጨረሰ፡ እንዲህ አለው፡ “መጥተህ፡ ማንን እንዳገኘን እይ፥ የዮሴፍን ልጅ፡ የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል። እኛ ስንፈልገው የነበረው መሲሕ እርሱ ነው” አለው።

አሁን ናትናኤል እንዲህ ሲል ይሰማኛል፡ “አሁን፥ ፊልጶስ፡ አላበድክም፡ አይደል? ”

131 “ኦህ፡ አይ። በፍጹም። አሁን ልንገርህ። ታውቃለህ፡ መጽሐፍ ቅዱስን አብረን ስናጠና ቆይተናል፡ ነቢዩ መሲሑ ምን እንደሚሆን ነበር የተናገረው? ”

“እርሱ ነቢይ እንደሚሆን ነው።”

“ዓሣ ከእርሱ ትገዛ የነበረውን ሰሙን ለመጻፍ እንኳን በቂ ትምህርት ያልነበረውን፡ ሰምዖን የተባለውን፡ ያንን አዛውንት ዓሣ አጥማጅ ታስታውሰዋለህ? ”

“እዎ። ኧ-ህ።”

132 “እርሱ መጣና። ምን እንደሆነ ታውቃለህ? ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሰሙ ሰምዖን እንደሚባል ነገረው፡ ሰሙንም ትርጉሙ ‘ትንሽ ድንጋይ’ ወደ ሆነው ወደ ጴጥሮስ ቀየረው፡ እንዲሁም አባቱ ማን እንደነበረ ነገረው።”

“መልካም፡” እ—እንዲህ አለ፡ “አላውቅም። ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን? ”

133 እርሱም፡ “ስለዚህ ጉዳይ አናውራ፥ ዝም ብለህ መጥተህ እይ” አለው። ያ ጥሩ ሀሳብ ነው፡ “መጥተህ እይ።”

ስለዚህ ፊልጶስ፡ ናትናኤልን ይዞ መጣ። እርሱም ሲመጣ፡ ምናልባት ኢየሱስ ቆሞ፡ እየተናገረ፡ ምናልባትም በጸሎት መሰመር ለቆሙ ታማሚዎች እየጸለየ ሊሆን ይችላል። ኢየሱስ ወዳለበትም በቀረበ ጊዜ፡ ኢየሱስ፡ ዘወር ብሎ ተመለከተውና፡ “እነሆ ተንኮል የሌለበት እውነተኛ እስራኤላዊ” አለው።

134 አሁን፡ እናንተ፡ “መልካም፡ ከአለባበሱ የተነሳ ነው” ትሉ ይሆናል። ኦህ፡ አይደለም። የምስራቅ ሰዎች ሁሉ ተመሳሳይ ነው የሚለብሱት። እርሱ ሶርያዊ፡ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ሊሆን ይችል ነበር፥ ጢሙ፡ ልብሱ።

135 እርሱም፡ “እነሆ ተንኮል የሌለበት እውነተኛ እስራኤላዊ” አለ፡ በሌላ አባባል፡ “እውነተኛና፡ ቅን ሰው” ማለቱ ነው።

መልካም፡ ይህ ናትናኤልን አበረደው። እርሱም፡ “ረቢ” አለ፡ ትርጉሙም፡ “መምህር” ማለት ነው። “ረቢ ሆይ፡ መቼ አውቀኸኝ ታውቃለህ? አይሁዳዊ መሆኔን እንዴት አወቅህ? እውነተኛና ተንኮል የሌለብኝ መሆኔንስ፡ እንዴት አወቅህ? ”

136 እርሱም፡ “ፊልጶስ ሳይጠራህ፡ ከበለስ በታች ሳለህ፡ አየሁህ” አለው። ኡህ! ከአሥራ አምስት ማይል ርቀት ላይ፡ በሀገሪቱ ማዶ፡ ከአንድ ቀን በፊት አየው።

ምን አለ? “ረቢ ሆይ፡ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ። አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ!”

137 ዳሩ ግን በዚያ የቆሙት፡ እነዚያ ራሳቸውን-የሾሙና፡ የተኮፈሱ-ካህናት፡ “ይህ ሰው ብዔልዜቡል ነው፡ ጠንቋይ ነው፡” አሉ።

ኢየሱስም፡ “ስለዚህ ነገር ይቅር እላችኋለሁ” አላቸው።

138 አሁን፡ አስታውሱ፡ ይህንን በድምፃቸው አውጥተው አልተናገሩትም፡ ነገር ግን በልባቸው ነበር ያሉት። “እርሱም አሳባቸውን አወቀ።” በትክክል። መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ያንን ነው። ከፈለጋችሁ **ቴሌፓቲ** በሉት፡ ነገር ግን እ—እርሱ አሳባቸውን አወቀ።

139 እርሱም እንዲህ አለ፡ “ስለዚህ ነገር ይቅር እላችኋለሁ። ነገር ግን አንድ ቀን መንፈስ ቅዱስ ይመጣና ይህንኑ ነገር ያደርጋል፡” እሱ ከሄደ በኋላ ነው፥ “በእርሱ ላይ ቃል የሚናገር ግን፡ በዚህ ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው አይሰረይለትም።” ልክ ነው? አሁን፡ እነዚያ አይሁዳውያን ነበሩ።

ከዚያም አንድ ቀን በሰማርያ ሊያልፍ አስፈለገው።

140 ነገር ግን ወደዚያ ከመሄዳችን በፊት፡ ሴትዮዋን እናገኛታለን፡ ወይም፡ ው—ውብ በሚባለው ደጃፍ ሲያልፍ፡ የተፈወሰውን፡ ሰውዬ እናገኛለን። ኢየሱስም ሁኔታውን አውቆ፡ “አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ፡” አለው። እርሱም እንደተባለው አደረገ፡ ተፈወሰም።

ቀጥሎም፡ አይሁዳውያን፡ አንዳንዶቹ እንደተቀበሉት ደርሰንበታል። አንዳንዶቹ አመኑ፥ አንዳንዶቹ ደግሞ አላመኑም። ለምን አላመኑም? ለሕይወት አልተመደቡም ነበርና ነው። የዚያ ባህርይ አካል አልነበሩም።

141 አሁን አስታውሱ፡ እነርሱ ካህናትና ታላላቅ ሰዎች ነበሩ። ኢየሱስ ግን… እስቲ እነዚያን የሥነ መለኮት ምሁራንና ካህናት አስቡ፡ በሕይወታቸው ውስጥ አንዳች እንከን ልታገኙባቸው የማትችሉ ሰዎች ነበሩ። ኢየሱስ ግን፡ “እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ፡ የእርሱንም ሥራ ታደርጋላችሁ” አላቸው። አክሎም፡ “ከእግዚአብሔር ብትሆኑ ኖሮ፡ ታምኑኝ ነበር። እኔን ማመን ካልቻላችሁ፡ የ—የማደርገውን ሥራ እመኑ፥ እነርሱ እኔ ማን እንደሆንኩ ይመሰክራሉና” አለ።

142 አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው፡” ይላል። ኢየሱስም፡ “በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል” ብሏል። ልክ ነው? አስተውሉ፡ አሁን ያ እውነተኛው መልከ ጼዴቅ ነበረ።

143 አሁን እንደገና፡ አስተውሉ፡ ሦስት የሰው ዘሮች ብቻ ነበሩ።

እኔ መለያየትን አራማጅ እንደሆንኩ ስናገር ሰምታችሁኛል። አዎ ነኝ። ክርስቲያኖች ሁሉ የመለያየት አራማጆች ናቸው፥ የቆዳ ቀለም መለያየት ሳይሆን፡ የመንፈስ መለያየት ነው። የአንድ ሰው የቆዳ ቀለም ከእርሱ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። በልደቱ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኗል። ነገር ግን ክርስቲያንን፡ እግዚአብሔር፡ “ለዩልኝ… ” “ከመካከላቸው ውጡ… ” እና የመሳሰሉትን ብሏል። እርሱ ትክክል ከስህተት፡ ከርኩሰት የሚለይ፡ የመለያየት አራማጅ ነው።

144 ነገር ግን አስተውሉ፡ በዚያን ጊዜ መለያየት ነበራቸው፡ የዘር መለያየት፡ እነርሱም ሳምራውያን ነበሩ።

መጽሐፍ ቅዱስን ካመንን፥ በምድር ላይ ሦስት የሰው ዘሮች ብቻ አሉ፥ እነርሱም፡ የካም፡ የሴምና፡ የያፌት ሕዝቦች ናቸው። ያም የኖኅ ሦስቱ ልጆች ናቸው። ሁላችንም የተገኘነው ከዚያ ነው። በትክክል። ያም ሁላችንንም ወደ አዳም ይመልሰናል፡ ይህም ሁላችንንም ወንድማማቾች ያደርገናል። መጽሐፍ ቅዱስ፡ "እግዚአብሔር የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ደም ፈጠረ" ይላል። በደም መስመር ሁላችንም፡ ወንድማማቾች ነን። ጥቁር ሰው ለነጭ ሰው ደም ሊሰጥ ይችላል፡ ወይም ነጩ ለጥቁሩ ሊሰጥ ይችላል። ነጭ ሰው ለ—ለጃፓናዊው፡ ቢጫ ሰው፡ ወይም ለህንዳዊው፡ ለቀዩ ሰው፡ ወይም ምንም-ይሁን ምን፡ ወይንም ለሌላ ለማንኛውም፡ የያፌት ዘር፡ ደም ሊሰጠው ይችላል፡ ምክንያቱም ሁላችንም ያው አንድ ደም ነንና። የቆዳችን ቀለም፡ የኖርንበት ሰፍራ፡ ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።

ነገር ግን መለያየት የሚመጣው፡ እስራኤልን ከግብፅ እንዳወጣቸው ሁሉ፡ እኛም ከዓለም ሰንወጣ ነው። ከዓለም ነገሮች የምንለየው በዚያን ጊዜ ነው።

145 አሁን፡ እነርሱ የካም፡ የሴምና፡ የያፌት ሰዎች ነበሩ። የዘር ሐረጋቸውን ወደ ኋላ ለመቁጠር ጊዜ ቢኖረን ኖሮ፡ የአንግሎ-ሳክሰን ሕዝብ፡ ከየት እንደመጣ ማየት ትችሉ ነበር። አሁን፡ ያ አይሁዳዊው ነበረ... በበለዓም ሥራና፡ በሞዓብ ምክንያት ከአሕዛብ ጋር በመጋባት፡ ግማሽ አይሁዳዊና ግማሽ አሕዛብ የሆነው፡ ሳምራዊው ነበረ። እነርሱ ሳምራውያን ነበሩ። እንዲሁም አይሁዳውያንና አሕዛብ ነበሩ።

አሁን፡ እኛ አንግሎ-ሳክሰኖች ከዚህ ከማንኛውም ነገር ጋር ምንም ግንኙነት አልነበረንም። በማንኛውም መሲሕ አላመንም፡ በሌላ በምንም ነገር አላመንም ነበር። መሲሕንም አንጠብቅም ነበር። እኛ በኋላ ላይ ነው የገባነው።

ኢየሱስ ወደ ገዛ ወገኖቹ መጣ፡ የገዛ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም። ለደቀ መዛሙርቱም፡ "በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ፡ ይልቁንም ወደ ጠፉት ወደ እስራኤል በጎች ሂዱ እንጂ" አላቸው። እርሱም ወደ ጠፉት ወደ እስራኤል በጎች ብቻ ሄደ። ተመልከቱ፡ በአይሁድ ፊት፡ ራሱን እንደ የሰው ልጅ ገለጠ። እነርሱ ግን አልተቀበሉትም።

አሁን፡ ሳምራዊው፡ ግማሽ አይሁዳዊና ግማሽ አሕዛብ በመሆኑ፡ እነርሱም አመኑ፡ መሲሑንም ይጠብቁ ነበረ።

እኛ ግን አልነበርንም። እኛ ጣዖታትን የምናመልክ፡ ዱላ በጀርባችን ያዘልን፡ አረማውያን ነበርን፥ አሕዛብ ማለት ነው።

146 ነገር ግን አሁን አንድ ቀን፡ ቅዱስ ዮሐንስ ምዕራፍ 4 ላይ፡ ወደ ኢያሪኮ በሚወርድበት መንገድ፡ በሰማርያ ሊያልፍ አስፈለገው። ዳሩ ግን በሰማርያ አድርጎ ወጣ። ወደዚያም ሲወጣ፡ ሲካር ከምትባል ከተማ ውጪ ባለው የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ተቀመጠ። ያም የውሃ ጉድጓድ፡ ወደዚያ ሄዳችሁ የምታውቁ ከሆነ፡ ልክ እዚህ እንዳለው ዓይነት ሰፋ ያለ እይታ ያለው ነው። በዚያም ሁሉም የሚመጡበት፡ የሕዝብ፡ የውሃ ምንጭ አለ። ሴቶችም በማለዳ መጥተው፡ ውሃ በማሰሮዎቻቸው ይቀዳሉ፡ አንዱን በራሳቸው ላይ፡ ሌላውንም በዳሌያቸው ላይ አድርገው፡ አንዲትም ጠብታ ሳያፈሱ፡ ቀጥ ብለው ይራመዳሉ፥ እርስ በርሳቸውም እያወሩ ይሄዳሉ። ስለዚህ፡ ሰዎቹ፡ ወደዚያ ይመጡ ነበር።

147 ይህ የሆነው ከቀኑ በአሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ ነበረ። ስለዚህ ምግባቸውን፡ የሚበሉትን እንዲገዙ፡ ደቀ መዛሙርቱን ወደ ከተማ ላካቸው። እነርሱም በሄዱበት ጊዜ...

148 ሰመ-ጥፉ አንዲት ሴት ነበረች፡ እሷን ዛሬ፡ የዝሙት አዳሪ፡ ወይም፡ ሴተኛ አዳሪ፡ ብለን እንጠራታለን። እጅግ ብዙ ባሎች ነበሯት። ስለዚህ ኢየሱስ እዚያ ተቀምጦ ሳለ፡ ይህቺ ሴት በአሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ ወጣች። አያችሁ፡ ልጃገረዶች በማለዳ የልብስ ማጠቢያ ውሃቸውን ለመቅዳት ሲመጡ አብራቸው መምጣት አትችልም ነበረ፥ እነርሱ ሁሉ እስኪ... እንደ ዛሬው ጊዜ አይቀላቀሉም ነበረ። እሷ የተገለለች ነበረች። ስለዚህም፡ ውሃ ለመቅዳት ወጣች፥ ያንንም አሮጌ መቅጃ ወሰዳ፡ ገመዱንም በማሰሮው ላይ አድርጋ፡ ወደ ታች ማውረድ ጀመረች።

በዚህ ጊዜ፡ "አንቺ ሴት፡ የምጠጣውን ሰጪኝ" የሚል ድምፅ ሰማች። አሁን፡ አስታውሱ፡ ይህ መልከ ጼዴቅ ነው። ይህ የትናንቱ፡ ኢየሱስ፡ የሰው ልጅ ነው።

149 ዘወር ብላ ስትመለከትም፡ አይሁዳዊ መሆኑን አየች። ስለዚህም፡ "ጌታዬ፡ አይሁዳዊ ከሳምራዊቷ ምንም ነገር መጠየቁ ተገቢ አይደለም። እኔ ሳምራዊት ሴት ነኝ፡ ስለዚህ ካለህበት ቦታ አልፈህ ነው የተናገርከው። እንደዚህ ያለውን ነገር ልትጠይቀኝ አይገባም ነበር። እኛ እርስ በርሳችን ምንም ግንኙነት የለንም" አለችው።

150 እርሱም፡ "ነገር ግን የሚያነጋግርሽ ማን እንደሆነ ብታውቂ ኖሮ፡ አንቺ ራስሽ የምጠጣውን ሰጠኝ ብለሽ ትጠይቂኝ ነበር" አላት።

እሷም፡ "እንዴት ልትቀዳ ትችላለህ? ጉድጓዱ ጥልቅ ነው፡ መቅጃም የለህም" አለችው።

151 እርሱም፡ "እኔ የምሰጠው ውሃ፡ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የሕይወት ውሃ ነው" አላት።

ሁኔታዋ ምን እንደሆነ እስኪደርስበት ድረስ አነጋገራት። ከዚያም... አሁን ምን እንዳላት ተመልከቱ፡ "ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነዪ" አላት።

እሷም፡ "ባል የለኝም" አለችው።

152 እርሱም፡ "እውነት ተናገርሽ፡ አምስት ባሎች ነበሩሽና፡ አሁን አብሮሽ ያለው የአንቺ አይደለም። ስለዚህ፡ በዚህ እውነት ተናገርሽ፡" አላት።

በዚያች ሴትና በነዚያ የካህናት ሰብሰብ መካከል ያለውን ልዩነት ተመልከቱ። እነዚያ ሁሉ የካህናት ሰብሰብ በአንድ ላይ ቢደመር ከሚያውቀው በላይ፡ እሷ ስለ እግዚአብሔር ታውቅ ነበር።

153 እሷም፡ "ጌታዬ፡ አንተ ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ" አለችው። እሷም፡ "ለአራት መቶ ዓመታት ነቢይ አልነበረንም። አሁን፡ መሲሑ እንደሚመጣ እናውቃለን። መሲሑም ሲመጣ፡ የሚያደርገው ይህንኑ ነው" አለች። የመሲሑ ምልክት ያ ነበር፡ እርሱ የሰው ልጅ ነበርና። "እርሱ ሲመጣ የሚያደርገው ይህንኑ ነው። አንተ የእርሱ ነቢይ መሆን አለብህ" አለችው።

154 እርሱም፡ "እኔ እርሱ ነኝ" አላት። ሌላ ማንም ያንን ሊል አይችልም ነበር።

155 የውሃ ማስሮዋን ጥላ ወደ ከተማ ሮጠች፡ እንዲህም አለች፡ “ያደረግኩትን ሁሉ የነገረኝን ሰው መጥታችሁ፡ እዩ። ይህማ መሲሑ አይደለምን? ”

አሁን አስታውሱ፡ በአሕዛብ ዘመን መጨረሻ ላይ ያንኑ ነገር እንደሚያደርግ ተስፋ ሰጥቶ ነበር።

አይሁዳውያን ያንን መሲሕ ለመጠባበቅ አራት ሺህ ዓመታት ነበሯቸው፡ እንደሚመጣና ሲመጣም ምን እንደሚያደርግ ሲማሩ፡ አራት ሺህ ዓመታት አልፈው ነበር፡ ነገር ግን ሊያዩት፡ ወይም ሊያውቁት አልቻሉም። እሆናለሁ ብሎ በተናገረው ልክ በመጽሐፍ ቅዱሳዊው መንገድ ራሱን በገለጠ ጊዜ፡ ቲዮፋኒ ሆኖ ከቆየ በኋላ ሥጋ ሆኖ በመካከላቸው ባደረ ጊዜ፡ ሊያዩት አልቻሉም፡ ሥራውንም የዲያብሎስ ሥራ ብለው ጠሩት።

156 አሁን፡ የሁለት ሺህ ዓመታት ትምህርት ነበረን። ከሐዋርያት በኋላ፡ በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በኩል ወርደን መጥተናል። ከዚያም በሮማ ካቶሊክ፡ በግሪክና፡ በመሳሰሉት በኩል ወርደን፡ እስከ ሉተር ዘመን፡ እስከ ዌስሊና፡ እስከ-ሌሎችም፡ ዘጠኝ መቶ የተለያዩ ድርጅቶች ድረስ መጥተናል። እስከ አሁን ድረስ፡ እነዚህን ሁሉ የትምህርት ዘመናት፡ አሳልፈዋል።

አሁን እርሱ የፍጻሜው ጊዜ ከመምጣቱ ጥቂት ቀደም ብሎ፡ የሰዶምና የገሞራ ሁኔታ ዳግመኛ እንደሚሆን፡ ተስፋ ሰጥቷል፡ “በሰዶም ዘመን እንደነበረ፡ በፍጻሜውም ጊዜ የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ እንዲሁ ይሆናል፡ የሰው ልጅ ራሱን ዳግመኛ ይገልጣል።” [በቴፕው ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]

“ገና ጥቂት ዘመን አለ ከዚህም በኋላ ዓለም አያየኝም፥ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፡ ምክንያቱም እኔ፡” የግል ተውላጠ ስም ነው፡ “እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ በእናንተም ውስጥ፡ እኖራለሁ። ከእናንተ ጋር እሆናለሁ።” እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው። አያችሁ?

157 አያችሁ፡ ትላንት ማታ ከሰበክሁት ሰብከት አንጻር፡ **ሳምራዊው**፡ በእርግጥ አጋር ነበር፡ አያችሁ፡ የተዛባው ምሳሌ ነው። **አይሁዳዊው** ሳራ ነበር፡ ወይም የሳራ-ዘር ነበር። ነገር ግን **አሕዛብ** የማርያም ናቸው፡ የንጉሣዊው ዘር፡ የአብርሃም ንጉሣዊ ዘር።

158 አሁን በተስፋ ቃሉ መሰረት፡ በዚህ በመጨረሻው ዘመን፡ ያው እግዚአብሔር፡ ያው ክርስቶስ፡ ወደዚህ ተመልሶ በመምጣት ራሱን እንደ የሰው ልጅ ይገልጣል።

ለምን? እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነውና። እነዚያን አይሁዳውያን፡ ያንን... የመሲሕ ምልክት ሰጥቷቸው አልፈው እንዲሄዱ ከፈቀደላቸው፡ ከዚያም ወደ አሕዛብ ትምህርት ማብቂያ ላይ መጥቶ በሥነ መለኮት ብቻ እንዲገቡ ቢፈቅድላቸው ኖሮ፡ እርሱ ፍትሐዊ አይሆንም ነበር። ያንኑ ነገር ማድረግ አለበት፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በዕብ-... ዕብራውያን 13፥8 ላይ፡ “እርሱ ያው ነው፡” ይላልና።

በሚልክያስ 4 ላይም፡ እንዲሁም በተለያዩ ክፍሎች ሁሉ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ቤተክርስቲያን ልክ ዛሬ እንዳለችው እንደምትሆንና፡ ዓለምም እንደዚሁ እንደምትሆን፡ ተስፋ ሰጥቷል።

159 ዛሬ ዓለምን ተመልከቱ። የሰዶምን ሁኔታ ተመልከቱ። በተለያዩ ስፍራዎች ያሉትን የምድር መናወጦች፥ እንዲሁም እየተከሰቱ ያሉትን ነገሮች ተመልከቱ። ቤተክርስቲያንንና በውስጧ ያለውን፥ የባቢሎን ምስቅልቅል ተመልከቱ። ወደ እሷ የተላከውን መልእክተኛ፥ ኦራል ሮበርትስንና ቢሊ ግራሃምን ተመልከቱ።

G-r-a-h-a-m፥ ለመጀመሪያ ጊዜ፥ ሰሙ እንደ አብርሃም፥ በh-a-m የሚያልቅ መልእክተኛ፥ ለቤተክርስቲያናት ሁሉ ተልኳል። A-b-r-a-h-a-m ሰባት ፊደላት አሉት። G-r-a-h-a-m ስድስት ፊደላት አሉት። እርሱ የት ነው ያለው? በዓለም ላይ ነው። ስድስት የሰው ቁጥር ነው። ሰው የተፈጠረው በስድስተኛው ቀን ነው። ሰባት ግን የእግዚአብሔር ቁጥር ነው።

160 አሁን ወደ ታች ወደ ሰዶም ያሉትን ተመልከቱ። በዚያም ለእነርሱ የሚናገሩ መልእክተኞቻቸው ነበሯቸው።

ነገር ግን ያ የአብርሃም ንጉሣዊ ዘር የት ነው ያለው? የእነርሱስ ምልክት የት አለ? እንዲህ ያለው፥ “በሰዶም ዘመን እንደነበረ፥” ብሎ የተናገረው ምልክት፥ እግዚአብሔር ወርዶ በሰው ሥጋ ተገልጦ፥ ከኋላው በድንኳኑ ውስጥ ሳራ በልቧ ምን እያሰበች እንደነበር የተናገረው፥ ያ ምልክት የት አለ፥ የአሕዛብ ዓለም በእሳት ከመጥፋቱ በፊት የተሰጠው የመጨረሻው ምልክት ነው።

መላው ዓለም ከመጥፋቱ በፊት ይህ የአሕዛብ መንግሥት በእግዚአብሔር እሳትና ቁጣ ከመጥፋቱ በፊት፥ ቤተክርስቲያን የመጨረሻዋን ምልክት አግኝታለች። ይህንን ታምናላችሁን?

161 ያ መልከ ጼዴቅ ሥጋ ነበረ፥ በሰው አካልም ራሱን ገለጠ፥ ከዚያም በኋላ እርሱ ሥጋ ሆነ። አሁንም፥ ዛሬ ማታ፥ እርሱ ትናንትና፥ ዛሬ፥ እስከ ዘላለምም፥ ያው ነው። ይህንን ታምናላችሁን?

162 ታዲያ፥ ትናንትና፥ ዛሬ፥ ያው የሆነው ይህ መልከ ጼዴቅ ማን ነው… “አባት አልነበረውም፥ እናት አልነበረችውም፥ ለቀኖቹ መጀመሪያ አልነበረውም፥ ለሕይወቱም ፍጻሜ አልነበረውም።” አብርሃምንም አገኘው፥ ምን ዓይነት ምልክትስ አደረገ? ከዚያም ሥጋ በሆነ ጊዜ፥ የፍጻሜው ዘመን ከመምጣቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ይህ ዳግመኛ እንደሚደገም ተናገረ። ይህንን ታምናላችሁን? እኔ አምነዋለሁ።

እንጸልይ።

163 ውድ አምላክ ሆይ፥ “ትናንትና፥ ዛሬ፥ እስከ ዘላለምም ያው፥” እንደሆንክ የተናገርከውን ቃልህን አምናለሁ። ጌታ ሆይ፥ በልቤ ቅንነት፥ አንዳች ነገር ሊፈጸም እንደሆነ እውቃለሁ። በትክክል ምን እንደሆነ ለይቼ ላውቀው አልችልም። ጌታ ሆይ፥ አንዳች ነገር ለመናገር እፈራለሁ። አንተ የአገልጋዮችህን ልብ ታውቃለህ።

164 በዘመናት ሁሉ አንተ ነገሮችን ስትልክ፥ ሰዎች ሳይረዱት የቀሩት፥ ሰንት ጊዜ ነው። ሰው እግዚአብሔር ስላደረገው ነገር ሁልጊዜ ያመሰግነዋል፥ እንዲሁም ታላላቅ ነገሮችን እንደሚያደርግ ይናገራል፥ ነገር ግን አሁን እያደረገ ያለውን ችላ ይላል። በዘመናት ሁሉ እንደዚሁ ነበር። የሮማ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ፓትሪክን እንደ እግዚአብሔር ነቢይ ማየት ለምን ተሳናት? ጆን ኦፍ አርክ፥ ነ— ነቢይት ሳለች ለምን ገደሏት፥ እንደ ጠንቋይስ ለምን አቃጠሏት? አባት ሆይ፥

ሁልጊዜ የሚያስተውሉት ነገሩ ካለፈ በኋላ ነው። ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ዓይን ትሰውረዋለህ። ለእነዚያ ካህናት፡ “የነቢያትን መቃብር ታስጌጣላችሁ፡ በዚያም የምታስቀምጧቸው እናንተው ናችሁ” ማለቱ ምንም አያስገርምም። ካለፉ በኋላ፡ ስህተታቸውን ያያሉ። ጌታ ሆይ፡ በማንኛውም መልክ ብትመጣ፡ ሁልጊዜ ያሳድዱሃል።

165 ዛሬ ማታ፡ አምላክ ሆይ፡ አንድ ጊዜ ብቻ እንድታደርገው፡ እጸልያለሁ። ነገ ወደ... ወደ ቱክሰን ልንሄድ ፕሮግራም አለን። በሌሎች የዓለም ክፍሎች፡ በሌሎች ከተሞች መስበክ አለብን። ነገር ግን፡ ውድ አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ማታ እዚህ በጭራሽ... የተሰበከውን ቃል የሰሙ፡ ነገር ግን ቃሉ ሲገለጥ አይተው የማያውቁ ሊኖሩ ይችላሉ።

በመጀመሪያ እንደጠየቅሁህ። እነዚያ ደቀ መዛሙርት፡ ቀለዮጳና ጓደኛው፡ ከኤማሁስ ሲመለሱ፡ በመንገድ ላይ እየሄዱ ሳሉ፡ ከትንሳኤህ በኋላ፡ አንተ ከቁጥቋጦው ውስጥ ወጥተህ ታነጋግራቸውና፡ ትሰብክላቸው ጀመር። እንዴት፡ እርሱም እንዲህ አላቸው፡ “እናንተ የማታስተውሉ፡ ልባችሁም የዘገየ። ክርስቶስ ይህንን መከራ ሊቀበልና፡ ወደ ክብሩ ሊገባ እንደሚገባው አታውቁምን? ” ነገር ግን አሁንም አላወቁትም ነበር። ቀኑን ሙሉ ከአንተ ጋር ተጓዙ፡ አሁንም ግን አላወቁህም ነበር። ነገር ግን አንድ ሌሊት...

ምሽት ሲሆን፡ ከእነርሱ ጋር እንድትገባ አስገደዱህ። ወደ ትንሿ ማረፊያ ገብተው በሮቹን በዘጉ ጊዜ፡ ከመስቀልህ በፊት ታደርገው እንደነበረው አንድ ነገር አደረግህ፡ እነርሱም የተነሳው ክርስቶስ እንደሆነ አወቁ። በቅጽበትም ከመጋረጃው ጀርባ ተሰወርክና ሄድክ። በፍጥነትም ሮጠው ለደቀ መዛሙርቱ፡ “ጌታ በእውነት ተነስቷል” ብለው ነገሯቸው!

166 አባት አምላክ ሆይ፡ አሁንም ሕያው እንደሆንክ አምናለሁ። እንደሆንክም አውቃለሁ። ይህንም ብዙ ጊዜ አረጋግጠህልናል። ጌታ ሆይ፡ ለእኛ አንድ ጊዜ ብቻ ዳግመኛ ልታደርገው ትችላለህን? በፊትህ ሞገስን አግኝተን እንደሆነ፡ አንድ ጊዜ ዳግመኛ ይሁን። እኔ አገልጋይህ ነኝ፥ እዚህ ያሉትም አገልጋዮችህ ናቸው። ጌታ ሆይ፡ የተናገርኩት ሁሉ ሲደመር... ከአንተ የምትወጣ አንዲት ቃል ብቻ በእነዚህ አምስት ምሽቶች፡ ወይም አምስት መልእክቶች ውስጥ ከተናገርኩት ሁሉ ትበልጣለች። አንዲት ቃል ብቻ ከአንተ ብትወጣ፡ ከሁሉ ትበልጣለች። ሕዝቡ እውነትን እንደነገርኳቸው ያውቁ ዘንድ፡ አትናገርምን፡ ጌታ ሆይ? አምላክ ሆይ፡ ይህ ይሁንልን። በኢየሱስ ስም ይህን እጠይቃለሁ፡ ይህን አንድ ጊዜ ብቻ። አሜን።

167 አሁን፡ እኔ አላውቃችሁም። አንዳንድ ሰዎችን አውቃለሁ። **እዚህ** የተቀመጠውን ይህንን ልጅ አውቀዋለሁ። **እዚያ** ጋ የተቀመጠውን ቢል ዳውችን አውቀዋለሁ። እፈልጋለሁ... ወንድም ብሌየር፡ ሮድኒ ኮክስ እዚህ አሉ። ወደ ውጪ ማየት አስቸጋሪ ነው።

በእርግጥ፡ **በዚህ** በኩል፡ በአሁኑ ሰዓት እኔ የማውቀው፡ ማንም ሰው እያየሁ አይደለም።

168 አሁን በእናንተ ዘንድ እንግዳ መሆኔን የምታውቁ ሰንቶቻችሁ እዚህ አላችሁ? ስለ እናንተ ምንም እንደማላውቅ የምታውቁ፡ እጆቻችሁን አንሱ፡ በሁለቱም በኩል እጆቻችሁን አንሱ።

ስለ እናንተ አንዳች የማላውቀው ነገር፡ ወይም አንዳች ችግር ያለባችሁ ስንቶቻችሁ አላችሁ? እባካችሁ እጆቻችሁን አውጡ።

አሁን፡ ስለ እናንተ አንዳች ነገር ማወቅ ለእኔ ፈጽሞ፡ በፍጹም የማይቻል ነገር ነው። አለበለዚያ፡ ግን፡ ከመንፈስ መገለጥ የመጣ መሆን አለበት።

በእነዚህ ምሽቶች ሁሉ፡ ዛሬ ማታም፡ እርሱ እንዳልሞተ ነግሬአችኋለሁ፥ እርሱ እዚህ አለ፡ ያንኑ ነገር ለማድረግም ተስፋ ሰጥቷል። እንዲሁም በሚልክያስ 4ና በቅዱስ ሉቃስ መሠረት፡ በመጨረሻው ዘመን ዘመን እንደሚመጣ ቃል ገብተዋል፡ በሕዝቡ መካከል እንደገና በሰው መልክ እንደሚታይና ተመሳሳይ ነገሮችን እንደሚያደርግ፡ ያንኑ የመሲሕ ምልክት እንደሚገልጥ፡ ተስፋ ሰጥቷል። መጽሐፍ ቅዱስ አንባቢያን የሆናችሁ፡ ይህ እውነት መሆኑን፡ ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? "አሜን፡" በሉ። [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—አርታዒ።] ሁላችሁም መጽሐፍ ቅዱስ አንባቢያን መሆን አለባችሁ።

169 አሁን፡ ዛሬ ለሰዎች ይህ እንግዳ እንደሆነ አውቃለሁ፡ ነገር ግን አሁንም እውነት ነው። የናዝሬቱን ኢየሱስን ያላወቁበትም ምክንያት ይኸው ነው። የቤተክርስቲያናቸውን የሐይማኖት መግለጫዎች ያውቁ ነበር፡ እርሱን ግን አላወቁትም። ዳሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስ በተናገረው መንገድ መጣ፡ የሥነ መለኮት ምሁር ሳይሆን፡ ካህን ሳይሆን። እንደ ነቢይ መጣ፡ የገዛ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም።

170 አሁን፡ እግዚአብሔር ቃሉን የሚጠብቅ ከሆነ፡ እኔም አጋጣሚ ሆኖ... በማውቀው ሰው ላይ ቢወድቅ፡ ያኔ ሌ—ሌላ ሰው እመርጣለሁ። እያችሁ፡ እኔ የማላውቀውን ሰው ነው የምፈልገው። እንድትጸልዩ እፈልጋለሁ።

171 አሁን፡ ተመልከቱ፡ በአንድ ወቅት ደዌ የነበረባት አንዲት ምስኪን ሴት ነበረች። ገንዘቧን ሁሉ ለሐኪሞች ጨርሳ ነበር፥ ምንም ሊረዷት አልቻሉም። በልቧም፡ "የዚህን ሰው ልብሰ ብቻ ብነካ፡ እድናለሁ" አለች። ታሪኩን ታስታውሳላችሁ? ሁሉም ወደ ኋላ ሊያስቀሯት ሞክረው ነበር፡ ዳሩ ግን ሰንጥቃ በመግባት ልብሱን ነካች፡ ከዚያም ተመልሳ ተቀመጠች።

172 አሁን በደምብ አዳምጡ። እርሱ ያንን ሲያደርግ፡ እሷ ያንን ስታደርግ፡ ኢየሱስ ዘወር ብሎ እንዲህ አለ፡ "ማን ነካኝ? "

173 በዚህ ጊዜ፡ ሐዋርያው ጴጥሮስ ገሰጸው። ምናልባትም እንዲህ ዓይነት ነገር ብሎት ሊሆን ይችላል፡ "ጌታ ሆይ፡ እንዲህ ያለ ነገር አትናገር። ሕዝቡ በአንተ ላይ አንዳች ችግር እንዳለ ሊያስቡ ይችላሉ። ምክንያቱም፡ ሥጋህን እንዲበሉና ደምህን እንዲጠጡ በጠየቅካቸው ጊዜ፡ ገና ድሮም አንዳች ችግር እንዳለብህ አስበዋል። አሁን ደግሞ፡ 'ማን ነካኝ' ትላለህ? እንዴ፡ ይኸው ሕዝቡ ሁሉ እየነካህኮ ነው።"

174 እርሱም፡ "አዎን፡ ነገር ግን ኃይል ከእኔ እንደወጣ አውቃለሁ" አለ። ያ የተለየ ዓይነት መንካት ነበረ። አሁን፡ ማንኛውም ሰው **ኃይል** ማለት "ጥንካሬ" እንደሆነ ያውቃል። "ደከመኝ፥ ኃይል ከእኔ ወጥቷል።"

ያቺንም ምስኪን ሴት እስኪያገኛት ድረስ በሕዝቡ መካከል ተመለከተ፡ ስለ ደም መፍሰሰዋም ነገራት። እሷም ያ የደም መፍሰሰዋ እንደቆመ በሰውነቷ

ታወቃት። ልክ ነው? እርሱም፡ “እምነትሽ አድኖሻል” አላት።

አሁን፡ በዚያ ያለው የግሪኩ ቃል **ሶዞ** ነው፡ ትርጉሙም አካላዊም ሆነ መንፈሳዊ ሙሉ በሙሉ “ዳነ፡” ማለት ነው፡ ያው ነው። እርሱ “አዳናት።” እ— እርሱ አዳኛችሁ ነው።

175 አሁን፡ ያ የትናንቱ እርሱ ከሆነ፡ በተሰፋ የተነገረው መሲሕ እርሱ መሆኑን፡ በሕዝቡ መካከል ለማረጋገጥ፡ ያደረገው ነገር ይህ ከሆነ፥ ራሱንም የገለጠው በዚህ መንገድ ከሆነ፡ ዛሬም ያንኑ ነገር እንደሚያደርግ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ተሰፋ ከሰጠ፥ ያ—ያንኑ ነገር ማድረግ አይጠበቅበትምን?

176 እናንተም፡ “ስለ በሽተኞች መፈወስ ተናገሮ ነበርን” ትሉ ይሆናል? አዎ!

አሁን ያነበብኩት መጽሐፍ ቅዱስ፡ ዕብራውያን፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን በድካማችን ስሜት ሊነካ የሚችል ሊቀ ካህናችን ነው፡” ይላል። ይህ እውነት መሆኑን ሰንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? መጽሐፍ ቅዱስ ያንን ተናግሯል። “በድካማችን ስሜት ሊነካ የሚችል ሊቀ ካህን ነው አሁን።” ታዲያ ያኔ የነበረው ያው ሊቀ ካህን ከሆነ፡ አሁን እንዴት ያደርጋል? ያው ሊቀ ካህን ከሆነ፡ ያኔ እንዳደረገው በተመሳሳይ መንገድ ማድረግ አለበት። አሁን፡ እናንተ ምናልባት...

እኔ ሊቀ ካህናችሁ አይደለሁም። እኔን ብትነኩኝ፡ ባላችሁን ወይም ወንድማችሁን፡ ወይም-ደግሞ፡ ሰውን እንደመነካት፡ ይቆጠራል።

177 ዳሩ ግን እምነታችሁ እርሱን እንዲነካው አድርጉ፡ ከዚያም የሚሆነውን ተመልከቱ። አሁን፡ እኔ የእግዚአብሔር አገልጋይ ከሆንኩና እውነትንም ከነገርኳችሁ፡ እግዚአብሔር ያ እውነት መሆኑን ያጸናዋል። ያም ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬ ማታ ሕያው እንደሆነና፡ እዚህም እንደቆመ ያረጋግጣል። ልክ ነው?

አሁን፡ እምነት ይኑራችሁ፡ አንዴ በአንድ በኩል ብቻ፡ በአንድ በኩል ብቻ። እዚያ ያላችሁ እምነት ይኑራችሁ። መሰማት ስለማይችሉ፡ እዚህ ማይክሮፎኑ አጠገብ ብቆይ ይሻላል።

178 አንድ ሰው ብቻ ወደ እግዚአብሔር ቀና ብሎ፡ እንዲህ ይበል፡ “እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህ ሰው አያውቀኝም። ስለ እኔ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም። ለእርሱ ፈጽሞ እንግዳ ነኝ። ዳሩ ግን ጌታ ሆይ፡ እምነቴ አንተን ይንካ። ጌታ ሆይ፡ ችግሬ ምን እንደሆነ አንተ ታውቃለህ። ስለ እኔ ሁሉንም ነገር ታውቃለህ። ጴጥሮስ ማን እንደነበረ እንዳወቅህ፡ ናትናኤልንም እንዳወቅህ፡ ደም ይፈሳት የነበረችውም ሴት ችግሯ ምን እንደነበረ እንዳወቅህ ሁሉ፡ እኔም ማን እንደሆንኩ ታውቃለህ። ይህ ሰው ደግሞ ‘ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው’ እንደሆንክ ነግሮኛል። እንደዛ ከሆነ፡ ጌታ ሆይ፡ እምነቴ አንተን ይንካ” በሉ።

እርሱም ያንን ቢያደርግ፡ እንዲሁም በማያሻማ ሁኔታ ራሱን እዚህ ቢያረጋግጥ፡ ቢያንስ ለምስክርነት ለአንድ፥ ወይም ለሁለት፡ ወይም ለሦስት ሰዎች ይህን ቢያደርግ፡ ሰ—ሰንቶቻችሁ፡ በሙሉ ልባችሁ ታምኑታላችሁ? [ጉባኤው፡ “አሜን” አለ።—አርታዒ።] እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

179 አሁን፡ አባት አምላክ ሆይ፡ ይህ ሙሉ በሙሉ ከማንም ሰው አቅም በላይ ነው። ይህ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ክስተት መሆን አለበት። ስለዚህ ጌታ ሆይ፡ አሁን እንድትረዳኝ እጸልያለሁ። እኔ በእጅህ ውስጥ ነኝ። መልካም መስሎ የታየህን በእኔ ላይ አድርግ። በኢየሱስ ስም። አሜን።

180 አሁን፡ አትረበሹ። ዝም ብላችሁ፡ በትህትናና በአክብሮት እንዲህ በሉ፡ "ጌታ ሆይ፡ አገለግልሃለሁ። ያም እውነት ይሆናል፡ ይህም፡ ልብስህን መነካት ከቻልኩ፡ በዚያ ሰው በኩል መልሰህ ትናገራለህ። ያም የተናገረው ነገር እውነት መሆኑን ያረጋግጥልኛል።" ልክ ነው?

181 የዚያን ብርሃን ፎቶግራፍ አይታችሁ የምታውቁ ስንቶቻችሁ ናችሁ? በሀገሪቱ ሁሉ፡ በየቦታው አለ። የሳይንስ ሰዎች ወስደው መርምረውታል፡ በሁሉም ቦታ አለ። አሁን፡ እርሱ አሁን እዚሁ አለ፥ ስለ **ጋብቻና ፍቺ** የተናገረው ያው እርሱ ነው፡ በዚያ ተራራ ላይ የነበረው፡ ኮረብታዎቹን ያናወጠው ያው እርሱ ነው፡ በ33 እዚህ ወንዝ ዳር የነበረው፡ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው የሆነው ያው እርሱ ነው። እርሱ ያው ነው።

182 አሁን፡ እዚች አንዲት ሴት አለች፡ አንዳች ነገር እንደተከሰተ አሁን ተገንዝባለች። ያ ብርሃን ልክ በእርሷ ላይ እያንዣበበ ነው። **እዚሁ** ተቀምጣለች፡ አረንጓዴ ሹራብ፡ ወይም እንደዚያ ዓይነት ነገር ለብሳለች። ሴትዮዋን አላውቃትም። እርስ በርሳችን እንግዳ እንደሆንን እሰባለሁ። ልክ ነው። እግዚአብሔር... የ—የአንድ ነገር ፍላጎት አለሽ፡ እግዚአብሔርም ችግርሽ ምን እንደሆነ ሊገልጥልኝ እንደሚችል ታምኛለሽ? ይህን ካደረገ፡ እኔ ስለማላውቅሽ፡ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ኃይል መሆን እንዳለበት ታውቂያለሽ። ከተፈጥሮ በላይ በሆነ መንገድ መምጣት አለበት።

ጉዳዩ ምን እንደሆነ በምታስቢው ላይ የተመሰረተ ነው። ከካህናቱ ጎን በመቆም፡ "ዲያብሎስ ነው" ልትይ ትችያለሽ፡ ወይም ከአማኞች ጎን በመቆም "የእግዚአብሔር ነው" ልትይ ትችያለሽ። ያመንሽው የትኛውንም ቢሆን፡ ሽልማትሽ የሚመጣው ከዚያው ነው።

183 እግዚአብሔር ችግርሽን ቢገልጥልኝ፡ እርሱን ለዚያ ችግርሽ እ—እንደ ማስተሰረያ አድርገሽ ትቀበይዋለሽን? ችግሩ ምን እንደሆነ አላውቅም። ዳሩ ግን አንዳች ነገር እየተከናወነ እንዳለ ግን፡ አውቃለሁ፡ አንቺም ታውቂያለሽ።

184 እ... አሁን፡ ምን እየተሰማሽ እንደሆነ ልንገርሽ፡ ከዚያም ታውቂያለሽ፥ እጅግ ሞቅ ያለ፡ ጣፋጭና፡ ምቹ የሆነ ስሜት ነው። ቀጥታ ወደ እርሱ እየተመለከትኩ ነው። ከሴትዮዋ ላይ እያንዣበበ ያለው ያ ብርሃን፡ የሚያብረቀርቀው ብርሃን ነው።

ሴትዮዋም በሆድ ህመም ችግር እየተሰቃየች ነው። በሆዷ ውስጥ፡ ልክ እንደ፡ ዕጢ ዓይነት ነገር ነው። የዚህ አካባቢ ሰው አይደለችም። አይደለችም። አንቺ የመጣሽው ከዚህ ራቅ ካለ ቦታ ነው አይደል? ልክ ነው። የመጣሽው ከዊስኮንሲን ነው። ልክ ነው? እርግጥ ነው። አሁን ተፈውሰሻል። እምነትሽ አድኖሻል።

185 አሁን ሴትዮዋ ማንን እንደነካች ንገሩኝ። እኔ ከእሷ ሃያ-አምስት ያርድ እርቄ ነው ያለሁት። እሷ የነካችው ኢየሱስ ክርስቶስን፡ ሊቀ ካህኑን ነው። ይህንን ታምናላችሁን?

186 ያነጋገርኳትን አንዲት ሴት እየተመለከትኩ ነው። ይህቺ ሴት፡ ቀጥታ እሷን እየተመለከትኳት ነው፡ ምክንያቱም ለአንድ ሰው አጥብቃ እየጸለየች ነውና። አንድ ሰው እንዳላት ነግራኛለች... ስለዚህ ጉዳይ ምንም የነገረችኝ ነገር የለም።

ስሟ ግን ወይዘሮ ዋልድሮፕ ነው። የመጣችው ከፊኒክስ ነው። ከሞት የተነሳች ናት፡ ሐኪሟም የኤክስ-ሬይ ምስሎችን ይዞ መጥቶ በልቧ ውስጥ ካንሰር እንደነበረ አሳይቷል። በጸሎት መስመር ውስጥ ሞታ ነበር። ያ ከሆነ ምን ያህል ጊዜ ሆነው፡ ወይዘሮ ዋልድሮፕ? ከአሥራ ሰምንት ዓመታት በፊት፡ እነሆ ዛሬ ማታ ሕያው ምስክር ሆና፡ በዚያ ተቀምጣለች። ሐኪሟም ወደ ስብሰባው መጥቶ፡ ያንን ይዞ መጥቶ... "ይህቺ ሴት እንዴት ልትኖር ትችላለች፡" አለ? ዳሩ ግን እነሆ እሷ በሕይወት አለች፡ የበሽታውም ምልክት እንኳ የለም።

187 አንድ ሰው ይዛ መጥታለች፡ ለእርሱም እየጸለየች ነው። አሁን፡ እርሱ በስኳር በሽታ ምክንያት፡ በመሞት ላይ ነው። አሁን፡ ያንን አውቄ ነበር። ዳሩ ግን እየጸለይሽ በመሆንሽ... ወይዘሮ ዋልድሮፕ፡ እርሱ ማን እንደሆነ እንደማላውቅ ታውቂያለሽ።

188 እርሱ የመጣው ከሚዙሪ ነው፡ ሰሙም ሚስተር ኩፐር ነው። ልክ ነው። አሁን፡ ካመንክ፡ ወዳጄ፡ ተመልሰህ ወደ ቤትህ ሄደህ ጤናማ ልትሆን ትችላለህ። ምርጫው ያንተ ነው፡ ካመንክበት።

189 እዚች አንዲት ሴት አለች፡ በአሰም በሽታና፡ በተወሳሰቡ ህመሞች እየተሰቃየች ነው። ከዚህ አካባቢ አይደለችም። እዚያ በሕዝቡ መሃል ተቀምጣለች፡ ልክ **እዚያ**። እሷም... የዚህ አካባቢ ሰው አይደለችም። የመጣችው ከጆርጂያ ነው። ሚስ ማኬኒ። እግዚአብሔር እንደሚፈውስሽ በማመን፡ በሙሉ ልብሽ ታምኛለሽን? ለእኔ እንግዳ ከሆንሽና፡ ያም እውነት ከሆነ በእግሮችሽ ቁሚ። ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሻል። ታምኛለሽን?

190 በጀርባዬ በኩል፡ ከኋላዬ የተቀመጠ አንድ ሰው አለ። እግዚአብሔርን እያገኘው ነው። ነገሩ፡ እርሱም የሚፈልገው፡ የልብ ችግር ያለበት ህፃን ልጅ አለው። ያ ህፃን በልቡ ውስጥ ያልተለመደ ድምፅ እንዳለበት፡ ሐኪሙ ተናግሯል። የዚያ ሰው ሰም ሚስተር ኮክስ ነው። ሚስተር ኮክስ፡ በእግርህ ቁም። "ከኋላው ሆና፡ ሳራ ምን እያሰበች እንደነበር ነገራት።"

191 ከእርሱ ፊት ለፊት በሌላኛው ረድፍ፡ ትንሽ ወደ ኋላ፡ ከዚህ አካባቢ ያልሆነ፡ ከኒው ሜክሲኮ የመጣ አንድ ሰው አለ። በሕይወቴ፡ አይቼው አላውቅም። አሁን ቀጥታ ወደ እርሱ እየተመለከትኩ ነው፡ እርሱም ከኋላዬ ነው። የመጣው ከኒው ሜክሲኮ ነው። ሰውዬውም አጥብቆ የሚያስብላት አንዲት ሴት ልጅ አለችው፡ ልጅቷም አፏ ላይ አንዳች ችግር አላት። እሱም... ችግሩ ያለው በላንቃዋ ላይ ነው። የሰውዬውም ሰም ሚስተር ዌሰት ነው። ወዳጄ፡ በእግርህ ትቆማለህን? ለእኔ ፈጽሞ እንግዳ ነው፡ ዳሩ ግን ጌታ አምላክ ልጁን ይፈውሳታል።

192 አሁን በሙሉ ልባችሁ ታምናላችሁን? ሰንቶቻችሁ አሁን በሙሉ ልባችሁ ታምናላችሁ? አሁን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው አይደለምን? አሁን እንደ አዳኛችሁ አድርጋችሁ ትቀበሉታላችሁን? እጆቻችሁን አንሱ። እንደ ፈዋሻችሁስ ታምኑበታላችሁን?

193 እዚህ፡ እዚህ ሽባ የሆነች ወይም የሆነ ችግር ያለባት፡ በቃሬዛ ላይ የተኛች፡ አንዲት ሴት አለች።

በዚህ ማይክሮፎን ልትሰሚኝ ትችያለሽን? አላውቅሽም። አንቺ በዚያ የተኛሽ አንዲት ሴት ብቻ ነሽ። ልፈውስሽ ብችልኖሮ፡ አደርገው ነበር። ልፈውስሽ አልችልም።

መልካም። እየተደሰተ ያለ አንድ ሰው ነው። ልጅቱ ተፈወሰችለት።

አላውቅሽም። አንቺ ሴት ነሽ፡ እኔ ደግሞ ወንድ ነኝ። በሕይወታችን ስንገናኝ ይህ የመጀመሪያችን እንደሆነ፡ እሰባለሁ። እነዚህ ሰዎች ናቸው… ? … ያመጡሽ። እውነቱን ለመናገር፡ ወደዚህ ስትመጪ ይህ የመጀመሪያሽ ነው፡ ገና አሁን ነው ያመጡሽ። የመጣሽው ከሩቅ መንገድ ነው። የሞት ጥላ አጥልቶብሻል። ካንሰር አለብሽ። ሽባነት አይደለም። ካንሰር ነው። ሐኪሞቹ ከዚህ በላይ ሊረዱሽ አይችሉም። እውነት ነው። በእርግጥም ትሞቻለሽ፥ እነዚያ ሐኪሞች ከዚህ በላይ ሊረዱሽ አይችሉም።

194 በአንድ ወቅት በሰማርያ በር ላይ የተቀመጡ ሦስት ለምጻሞች ነበሩ። እነዚያም ለምጻሞች፡ "እስክንሞት ድረስ ለምን እዚህ እንቀመጣለን" አሉ? ምክንያቱም በዚያ ከነበረው በሽታ፡ ከረሀብና፡ እርስ በርሳቸው የገዛ ልጆቻቸውን ከመብላታቸው የተነሳ ነው። እነርሱም፡ "ወደ ጠላት ሰፈር፡ ወደ ሶርያውያን ብንወርድ፥ ቢገድሉን፡ ያው፡ እንሞታለን። በሕይወት ከተዉን ግን፡ እንኖራለን" አሉ። ያንንም አጋጣሚ ተጠቀሙበት። በዚያም እምነት፡ ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን፡ መላውን ሕዝብ አዳኑ።

195 አሁን፡ እዚያው ከተኛሽ ትሞቻለሽ። ዳሩ ግን ወደ ጠላት ሰፈር እንድትሄጂ አልተጠየቅሽም። ይልቁንም ወደ አባት ቤት ተጋብዘሻል፥… ? …

196 በካንሰር እየሞትሽ ነው። ያለ እግዚአብሔር ልትኖሪ አትችዪም። የዚህች ከተማ አይደለሽም። የዚህ አካባቢ አይደለሽም። የመጣሽው ከሩቅ መንገድ ነው። የመጣሽው ከሚልዋኪ ነው። እውነት ነው። ልክ ነው። ከተማዋን አይቻታለሁ። አውቃታለሁ። ልክ ነው።

ታምኛለሽን? አሁን እግዚአብሔርን እንደ ፈዋሽሽ አድርገሽ ትቀበይዋለሽን? ፈቃደኛ ከሆንሽ፡ ምንም ያህል የደከምሽ ቢሆን፡ ምንም ያህል በአልጋ ላይ የዋለሽ ብትሆኚም፡ እኔ ባንቺ ቦታ ብሆን ኖሮ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እቆም ነበር ብዬ፡ እምናለሁ። ያንንም ቃሬዛ ተሸክሜ ወደ ቤት በመሄድ፡ ለእግዚአብሔር ክብር እኖር ነበር። እንደ እግዚአብሔር ነቢይ፡ ትታዘዢኛለሽን? እንግዲያውስ ተነሺና ሂጂ። ደህና ሁኚ! አትፍሪ። ከቃሬዛው ላይ ተነሺ፥ እግዚአብሔር ጤናማ ያደርግሻል። አያችሁ?

197 መነሳትና ብርታት ማግኘት ትችል ዘንድ አንድ ሰው ይደግፋት። በእግዚአብሔር ታምናላችሁን? ጥቂት ብርታት እስክታገኝ ተዉአት፥ ደህና ትሆናለች። ያ ነው በቃ፡ እህቴ። በጌታ በኢየሱስ ስም፡ እነሆ እሷ ቆመች!

ሁላችንም ቆመን ለእግዚአብሔር ምስጋናን እንስጥ። እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው!

ሂጂ፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይባርክሽ። ደህና ሁኚ።

65-0221E ይህ መልከ ጼዴቅ ማነው?
ፓርክቪው ጁኒየር ሀይ ስኩል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ:

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org